# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

81ኛ ዓመት ቁጥር 259 ግንቦት 19 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# ‹‹የኢትዮጵያ እና ናይጄሪያ ትብብር መጠናከር ለአህጉራዊ ትብብር ወሳኝ ነው››

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ

## - ጠቅላይ ሚኒስትሩ በኅብረቱ የመሪዎች ጉባኤ ላይ ለመሳተፍ ማላቦ ይገኛሉ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ እና ናይጄሪያ ትብብር መጠናከር ለአህጉራዊ ትብብር ወሳኝ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ተናገሩ።

በናይጄሪያ የሁለት ቀናት ይፋዊ የሥራ ጉብኝት ያደረጉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ፣ ጉብኝቱን አጠናቀው በአፍሪካ ኅብረት ልዩ የመሪዎች ጉባኤ ላይ ለመሳተፍ ከልዑካን ቡድናቸው ጋር ትናንት ወደኢኳቶሪያል ጊኒ ማላቦ አምርተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አሶ ሮክ በተሰኘው የፕሬዚዳንት ቤተ መንግሥት ሲደርሱ በፕሬዚዳንት ሞሐመዱ ቡሃሪ ደማቅ አቀባበል ተደርጎላቸዋል።

በመቀጠልም በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የተመራው ልዑክ ከናይጄሪያ ልዑካን ቡድን ጋር የሁለትዮሽ ውይይት አድርጓል።

ከውይይቱ በኋላም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት ጽሑፍ፣ ኢትዮጵያ እና ናይጄሪያ ታላላቅ የአፍሪካ አገራት መሆናቸውን ጠቁመው፣ «የእኛ ትብብር መጠናከሩ ለሁለትዮሽ

“የኢትዮጵያ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# መከላከያ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለመጠበቅ በተጠንቀቅ ላይ መሆኑን አስታወቀ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና አንድነት ለመጠበቅ በተጠንቀቅ ላይ እንደሚገኝ መከላከያ ሰራዊት አስታወቀ።

በመከላከያ ሰራዊት የምዕራብ ዕዝ 22ኛ ንስር ክፍለጦር የላቀ ውጤት ላስመዘገቡ አመራሮችና የሰራዊት አባላት የማዕረግ ዕድገት፣ ሜዳይና የዕውቅና ሽልማት ተሰጥቷል።

በወቅቱ የጦር ኃይሎች ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ እንዳስታወቁት፣ ሰራዊቱ አሁንም ኢትዮጵያን ለመጠበቅ በተጠንቀቅ ላይ ይገኛል።

ሰራዊቱ የድል ምልክት ነው። አገራችንን ሊያጠቃ የሚመጣውን

መከላከያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ለሠራዊቱ አባላት የማዕረግና ሜዳይ ሽልማት ተሠጥቷል


ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18 ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ



ኦሮሚያን ይጎብኙ

የብዝሃ-ውበት ምድር!



Website: https://www.visitoromia.org
Facebook: https://www.facebook.com/visitoromia/
Instagram: https://instagram.com/VisitOromia
Twitter: https://twitter.com/VisitOromia
LinkedIn: https://linkedin.com/company/visitoromia
YouTube: https://YouTube.com/visitoromia
Pinterest: https://Pinterest.com/visit_oromia
Telegram: https://t.me/visit_oromia

ኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን
www.visitoromia.org



Medhin Decor



የተንጣለለ ድንቅ የሰርግ አዳራሽ ከነ ሙሉ የውበት ስራ
የተሟላ የምግብ ዝግጅት ከሙሉ መስተንግዶ ጋር

Medhin Decor
ለሠርግ ለልደት እንዲሁም ለልዩ ልዩ ዝግጅቶች

አድራሻ 1ኛ ቦሌ ጌቱ ኮሜርሻል ጀርባ
2ኛ ከቃሊቲ ማሰልጠኛ አለፍ ብሎ ቆርኪና ጣሳ ፋብሪካ ገባ ብሎ
Contact Us 0911222993/ 0911208918


## በደቡብ ክልል የተጀመረው ሕግ የማስከበር ተግባር ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተገለጸ

ገጽ 4

## የሕወሓት ቡድን የሥልጣን ዘመኑን ለማራዘም አሁንም ሕዝቡን ለማሳሳት እየሞከረ ነው

ገጽ 4





UNIC ETHIOPIA
ሕብረት ኢንሹራንስ አማ
THE UNITED INSURANCE COMPANY SC
Tomorrows Company Today'
ለ ሁሉም የመድን ፍላጎትዎ
ለህይወት
ህጋዊ ግዴታዎ
ለንብረት
+251 111 26 34 34
@united.insurance@unic-ethiopia.com
7469

# ኢንዱስትሪውን የሚያዘምን ፖሊሲ በቅርቡ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ይጸድቃል ተብሎ ይጠበቃል

ተስፋ ፈሩ

አዲስ አበባ፡- ቀረጻው ተጠናቆ ውይይቶች የተካሄዱበት አዲስ የኢንዱስትሪ ፖሊሲ በቅርቡ በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንደሚጸድቅ ፕላንና ልማት ሚኒስቴር አስታወቀ።

የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር ፍጹም አሰፋ ከዘመን መጽሔት ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደገለጹት፣ ቀረጻው ተጠናቆ ብዙ ውይይቶች የተደረጉበት በቅርቡ በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንደሚጸድቅ የሚጠበቀው አዲስ የኢንዱስትሪ ፖሊሲ በአስር አመቱ የልማት ዕቅድ በአገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው የተወጠኑ እቅዶችን ለማሳካት ትልቅ እገዛ ያደርጋል።

ሚኒስትሯ አዲሱ የኢንዱስትሪ ፖሊሲ የእይታ ለውጦች እንዳሉት ተናግረዋል። ፖሊሲው ኢንዱስትሪ ተነጥሎ ብቻውን ሳይሆን ከሌሎቹ ዘርፎች ጋር ተሳስሮ መልማትና መተሳሰር እንዳለበት አምኖ የተነሳ መሆኑን በመግለጽ ግብርና ለኢንዱስትሪው ግብዓት ማቅረብ ካልቻለ አግሮፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪውና ሌሎችም ኢንዱስትሪዎች ሊለሙ አይችሉም፤ የማዕድን ዘርፉ ግብዓት ማቅረብ ካልቻለ የኢንዱስትሪው ዘርፍ ሊለማ አይችልም ስለዚህ አዲሱ ፖሊሲ በእነዚህ ዘርፎች መካከል ያለውን ትስስር በከፍተኛ ሁኔታ ማገናዘቡን እና እውቅና መስጠቱን ገልጸዋል።

አዲሱ ፖሊሲ በኢንዱስትሪው ውስጥ ከታች ወደላይና ከላይ ወደታች ሊኖር የሚገባውን ትስስር ታሳቢ ያደረገ ነው ያሉት ዶክተር ፍጹም፣ ይህ አሁን በኢንዱስትሪ ፓርኮቻችን ውስጥ በፈለግነው መጠን ያልሄደልን ነገር ነው። አንድ ሸሚዝ የሚያመርት ትልቅ ፋብሪካ የሸሚዙን ኮሌታ «የሸሚዙን አዝራር እና ለሸሚዙ ግብዓት የሚሆኑ ከጥጥ ጀምሮ ያሉ ግብዓቶችን በትስስር እዚሁ ካሉ አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች እንዲቀበልና እንዲሠራ እንፈልጋለን።


ፎቶ፡-ገበዘ ገብሬ
ዶክተር ፍጹም አሰፋ

በተወሰነ ደረጃ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ቢኖሩም ገና ብዙ ይቀረናል» ብለዋል።

አያይዘውም «የኢንዱስትሪ አብዮት ይመጣል እያልን ነው፤ ይህ አብዮት ዲጂታል አብዮት ነው። ይህንን የዲጂታል አብዮት ዛሬ ላይ አስበንበት ካልተዘጋጀን ሲመጣ እንደርስበታለን ማለት አንችልም። ኢትዮጵያ ይህንን ማጣት የለባትም። ከዚህ በፊት የነበሩትን የኢንዱስትሪ አብዮቶች አጥታለች። ስለዚህ አዲሱ የኢንዱስትሪ ፖሊሲ አራተኛውን የኢንዱስትሪ አብዮትም ታሳቢ ያደረገ ነው» ብለዋል።

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ዋና ባለቤትነት እየተመራ ያለው አዲስ ፖሊሲ ላይ የሚመለከታቸው መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት እንዲሁም ባለሙያዎች አስተያየት ሰጥተውበታል። ከተሳትፎና ከውይይት አልፎ በደንብ የተደራጀ ግብዓት የተደረገበትም ነው። አሁንም በዚያ የመኀልበት ሂደት ውስጥ ያለ ሲሆን ኢትዮጵያ በአጭር ጊዜ ውስጥ በጣም ጥሩ የሚባል የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ይኖራታል።


ፎቶ፡ ኢዮብ ተፈሪ
አቶ ሌንጮ ለታ

## ብሔራዊ ምክክሩ በሕዝቦች መካከል መተማመንን በመፍጠር ሰላምን ሊያሰፍን እንደሚችል ተገለጸ

ገመቹ ከድር

አዲስ አበባ፡- ብሔራዊ ምክክሩ በመሠረታዊ ጉዳዮች መግባባት ላይ ለመድረስ እና በሕዝቦች መካከል መተማመንን በመፍጠር ሰላምን ሊያሰፍን የሚያስችል የዴሞክራሲ ሥርዓት ለመገንባት እንደሚያስችል ፖለቲከኛ አቶ ሌንጮ ለታ ተናገሩ።

አቶ ሌንጮ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ብሔራዊ ምክክሩ በሕዝቦች መካከል መተማመን እና መግባባትን በመፍጠር ሰላምን ያሰፍናል። የዴሞክራሲ ሥርዓት ለመገንባት ያስችላል።

ሂደቱ በሕዝቦች መካከል መተማመን እና መግባባትን በማጠናከር ሰላም ለማስፈን የጎላ ሚና እንደሚኖረው፤ በግጭት አካባቢዎች ሰላም በማውረድ፣ ሰላም በሰፈነባቸው አካባቢዎች ደግሞ ከሁሉም አካላት ጋር በቅንጅትና በትብብር ለመሥራት እንደሚያስችል አመልክተዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ብሔራዊ ውይይቱ ሰላምን የሚያሰፍን የፖለቲካ ሥርዓት ለመገንባት ምቹ ሁኔታን በመፍጠር መተማመንና መግባባት ላይ እንዲደረስ ያደርጋል።

ሠላም በደፈረሰባቸው አካባቢዎች የግጭታቸውን ምክንያት በመለየት መፍትሄ እንዲያገኙ እና ሠላም እንዲሰፍን መሥራት እንደሚያስፈልግም የጠቆሙት አቶ ሌንጮ፤ በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ባለመግባባት የተፈጠሩ ፖለቲካዊ አለመግባባቶች በአብዛኛው በአገራዊ ምክክሩ መፍታት እንደሚቻል እምነታቸው መሆኑንም ተናግረዋል። ኢትዮጵያ ምን ዓይነት ሕዝቦች ያላት አገር ናት? ምን ዓይነት የዴሞክራሲ ሥርዓት ያስፈልጋታል? የሚሉትና መሰል ጉዳዮች መተማመን፣ ምላሽና መግባባት ላይ ሊደረስ ይገባል። ይህ ካልሆነ ሰላም የሚያሰፍን ሥርዓት መገንባት ያስቸግራል ብለዋል አቶ ሌንጮ።

ሠላም በደፈረሰባቸው አካባቢዎች በመሠረታዊ ፖለቲካዊ ጉዳዮች መግባባትና መተማመን ላይ መድረስ እንደሚገባ አመልክተዋል። በሁሉም አካባቢዎች ሰላም ማስፈንና ማጠናከር ይገባልም ብለዋል።

በአገራዊ ምክክሩ መግባባት ላይ መድረስ ወሳኝ ነው፣ የግጭት ምንጮችን ለይቶ ማጥናት፣ የሕግ የበላይነት ማስከበር ከመንግሥት ይጠበቃል። የተለመደውን ሳይሆን ዛሬ ኢትዮጵያ ያለችበትን ሁኔታ ያገናዘበ አዳዲስ ሀሳቦችን አመንጭቶ ማቅረብ ከምሁራን እንደሚጠበቅም አቶ ሌንጮ ገልጸዋል።



## በአሸባሪው ሕወሓት ቁጥጥር ስር የሚገኙ ዜጎች ለእንግልት እየተዳረጉ መሆኑን የዋግኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር አስታወቀ

ፍቃዱ ዴሬሳ

አዲስ አበባ፡- በአሸባሪው ሕወሓት ቁጥጥር ስር በሚገኙ አካባቢዎች የሚኖሩ ዜጎች ለእንግልት እየተዳረጉ መሆኑን የዋግኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር አስታወቀ።

የዋግኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ዋና አስተዳዳሪ አቶ ስቡህ ገበያው በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፣ በዞኑ ይተዳደሩ የነበሩ አበርገሌና ጻግብጂ ወረዳዎች ሙሉ በሙሉ እንዲሁም የሰቆጣ ወረዳ አንድ ቀበሌና ዝቋላ ወረዳ ስድስት ቀበሌዎች እንዲሁም ሌሎች አካባቢዎች በአሸባሪው ሕወሓት ቁጥጥር ስር በመሆናቸው በነዚህ አካባቢ የሚኖሩ ዜጎች ለተለያየ ችግሮች ተጋልጠዋል።

የሽብር ቡድኑ ጻግብጂ ወረዳ በሚገኝ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ላይ ጋዝ በማርከፍከፍ ማውደሙንም አስታውቀዋል። ቡድኑ በአካባቢው የሚገኝ በርካታ ንብረትና እንስሳትን የመዝረፍ ተግባር ላይ መሰማራቱንም አንስተዋል።

በሽብር ቡድኑ ስር የሚገኙ አካባቢዎች የሚኖሩ ዜጎች ላይ የሚደርሰው እንግልትና ሰቆቃ ያልቆመ መሆኑን የተናገሩት ዋና አስተዳዳሪው፣ የአካባቢዎቹን መሠረተ ልማቶች በማውደም፣ ሰዎችን በመግደልና በማፈናቀል እንዲሁም በማስፈራራት ሕዝቡ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንዲኖር ማድረጉን ተናግረዋል።

በሰብአዊ ድጋፍ ላይ የተሰማሩ የግብረሰናይ ድርጅቶችና ዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ ለትግራይ ሕዝብ ከሚያቀርበው ድጋፍ ባሻገር በተጠቀሱት አካባቢዎች አስፈላጊ የእርዳታ ቁሳቁስና እርዳታዎች እያደረገ ባለመሆኑ ማኅበረሰቡ ለከፍተኛ ችግር እየተጋለጠ መሆኑን አስታውቀዋል።

በሌላ በኩል በሽብር ቡድኑ ስር ከሚገኙ ስፍራዎች የተፈናቀሉ ዜጎች ከ88ሺህ በላይ የሚሆኑት በሰቆጣ ከተማ ብቻ እንደሚገኙ የገለፁት ዋና አስተዳዳሪው፣ ተፈናቃዮቹ በአብዛኛው ከአበርገሌና ጻግብጂ ወረዳዎች የተፈናቀሉ ሲሆኑ፣ ከሌሎች ወረዳዎች በተለይም ዝቋላ፣ ሰቆጣ ወረዳ፣ ኮረም፣ ዛታና አፍላ አካባቢዎች እንደሚገኙበት ተናግረዋል።

የአገር ውስጥና የውጭ ተራድኦ ድርጅቶች ርብርብ በማድረግ ለተፈናቃይ ማኅበረሰብ በተቻለ አቅም እርዳታ እያቀረቡ ይገኛሉ። በሰብአዊ ጉዳዮች ላይ የሚሠሩ ተቋማትን ጨምሮ የክልሉና የፌዴራሉ መንግሥት አስፈላጊ እርዳታዎችን እያቀረቡ እንደሚገኙም ጭምር ጠቁመዋል።

በቀጣይ የክረምት ወራት የመጠለያ፣ የተላላፊ በሽታ ወይም ወረርሽኝና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች እንደ ዋነኛ ችግር ሆነው የሚዘልቁ መሆናቸውን አንስተዋል።

በተለይ ደግሞ በክረምት ወቅት ተፈናቃዮች ወደ ቀያቸው ተመልሰው ሰብላቸውን በማሳቸው የሚዘሩበት ሁኔታ ካልተፈጠረ በቀጣይ ዓመት ለዳግም ተረጂነት መጋለጣቸው አይቀሬ መሆኑን አስታውቀዋል።

በመሆኑም መንግሥት በአጭር ጊዜ ውስጥ የድንኳንና ተሽከርካሪ እንዲሁም ሌሎች ከክረምት መግባት ጋር ተያይዘው ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን በማጤን ትኩረት እንዲሰጠው ብለዋል።

ለተፈናቃይ ይውላል ተብለው የሚቀርቡ ድጋፎ በፍትሃዊነት ለማዳረስ የዞኑ አመራር ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን ዋና አስተዳዳሪው አስታውቀዋል።

ዜና

# የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ዘርፉን ለማዘመን በትኩረት እየተሠራ መሆኑ ተገለፀ

* 2 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር የሎጅስቲክስ ወጪን ማዳን ተችሏል

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ዘርፍን ለማዘመን በትኩረት እየተሠራ እንደሆነ የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር ገለፀ።

የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር ሚኒስትር ወይዘሮ ዳግማዊት ሞገስ፤ በትናንትናው ዕለት ለኢፌዴሪ 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 1ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 10ኛ መደበኛ ስብሰባ የ2014 በጀት ዓመት የአሥር ወራት ሪፖርት አቅርበዋል። ሪፖርቱን ሲያቀርቡ እንደገለፁት፤ የትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ዘርፍ በቴክኖሎጂ የዘመነና የተቀላጠፈ በማድረግ ለሕዝቡ ተደራሽ እንዲሆን የተለያዩ ሥራዎች ተሠርተዋል።

የትራንስፖርት ዘርፉ በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ እና ልውውጥ ሥርዓት ባለመደራጀቱ እንዲሁም በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ባለመደገፉ በውስብስብ ችግሮች እንዲዋጥ ሆኗል ያሉት ሚኒስትሯ፤ ይህን ችግር ለመቅረፍ ትኩረት ተሰጥቶ ተሠርቷል ብለዋል።

በተሠሩት ሥራዎችም የሞደርናይዜሽን ሲስተም ተዘርግቶ 74 ሺህ 173 ሰዎች የትራንስፖርት አገልግሎት በበይነመረብ አግኝተዋል ተብሏል። በተጨማሪም የተቀናጀ የትራንስፖርት መተግበሪያ ሥርዓት ዘመኑ የሚጠይቀውን ቴክኖሎጂ እንዲያካትት ተደርጎ በማልማት በተያዘው በጀት ዓመት ወደሥራ እንዲገባ መደረጉን ሚኒስትሯ ገልፀዋል።

የትራንስፖርት ሚኒስትሯ ባቀረቡት ሪፖርት እንደገለፁት፤ በበጀት ዓመቱ ወደሥራ የገባው ይህ


ፎቶ: ገባቦ ገብሬ
ወይዘሮ ዳግማዊት ሞገስ

የተቀናጀ የትራንስፖርት መተግበሪያ ሥርዓት በጭነት ትራንስፖርት ዘርፍ መሠማራት ለሚፈልጉ የኦንላይን አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን በተጨማሪም አዲስ የትራንስፖርት ብቃት ማረጋገጫ ለማውጣት እና ዓመታዊ ብቃት ማረጋገጫ ለማደስ እንዲሁም ሌሎች አገልግሎቶች ማግኘት የሚያስችል ነው።

በማሪታይም አገልግሎት ተመሳሳይ ሥራዎች እየተሠሩ እንዳሉ የገለፁት ወይዘሮ ዳግማዊት፤ ከ4 ሺህ በላይ የመርከብ ካፒቴኖች፣ መሀንዲሶች እና ሌሎች ሙያተኞች በኦንላይን አገልግሎት ማግኘት መቻላቸውን ተናግረዋል።

በተመሳሳይ የሎጅስቲክስ ወጪዎችን በአገር ውስጥ ሥራዎች ለማዳን ሥራዎች ሲከናወኑ ነበር ያሉት ሚኒስትሯ፤ በበጀት ዓመቱ በአሥር ወራት ውስጥ በአጠቃላይ 2 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር የሎጅስቲክስ ወጪ ማዳን መቻሉን አብራርተዋል።

ይህ ሊገኝ የቻለው ቀድሞ በጅቡቲ ይታሹ የነበሩትን ኮንቴነሮች በአገር ውስጥ በማሸግ፤ አማካይ የመርከቦችን የወደብ ላይ ቆይታ በማሳጠር፤ የባሕር ወደብ አጠቃቀምን በማስፋት እና ደረቅ ወደቦችን በመጠቀም ነውም ብለዋል።

በዚህም ዕቃዎች ጅቡቲ ሄደው ቢታሹ ይወጣ ከነበረው ወጪ ከ2 ነጥብ 06 በላይ መዳኑን፤ የመርከቦች የወደብ ላይ ቆይታ ከ15 ቀናት ወደ ዘጠኝ ቀናት ዝቅ ማለቱን እና የሌሎች ሥራዎች ድምር ውጤት የሎጅስቲክስ ወጪ ላይ አወንታዊ ውጤት መጫወታቸውን ሚኒስትሯ ገልፀዋል።

ወይዘሮ ዳግማዊት፤ በባቡር የማጓጓዝ አገልግሎትም 1 ነጥብ 34 ቶን ዕቃዎችን በማጓጓዝ 1 ነጥብ 39 ቢሊዮን ብር መገኘቱን አብራርተው፤ በኢትዮ ጅቡቲ ባቡር 108 ሺህ መንገደኞችን ወደተለያዩ መዳረሻዎች ማጓጓዝ ተችሏል ብለዋል።

በበጀት ዓመቱ አሥር ወራት ከ7 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ባለሙያዎች የአቪየሽን ላይሰንስ መሰጠቱን እና ለ143 አውሮፕላኖች የበረራ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መሰጠቱን ያብራሩት ሚኒስትሯ፤ ከአቪየሽን ዘርፉ አገልግሎት በተለይም ከኤርናቪጌሽን አገልግሎት 1 ነጥብ 942 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገቢ ተገኝቷል ብለዋል።

የትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር ሚኒስትር ወይዘሮ ዳግማዊት፤ ዘርፉን ለማዘመን መንግሥት ባለው ቁርጠኝነት የ30 ዓመት የትራንስፖርት ማስተር ፕላን በማዘጋጀት የመጨረሻ መዕራፍ ላይ መድረሱን ገልፀዋል።

# ኢትዮ ቴሌኮም አገልግሎቶቹን በራይድ ትራንስፖርት አሽከርካሪዎች በኩል እንደሚያቀርብ አስታወቀ

መዓዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮ ቴሌኮም የራይድ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ አሽከርካሪዎችን በወኪልነት በመጠቀም የተለያዩ አገልግሎቶቹን ደንበኞች ያሉበት ድረስ እንደሚያቀርብ አስታወቀ።

ኢትዮ ቴሌኮም ከሀይብሪድ ዲዛይንስ የራይድ ትራንስፖርት አገልግሎት ጋር የቴሌኮም አገልግሎቶችን ለማቅረብና ክፍያዎችን በቴሌ ብር ለመፈጸም የሚያስችል የአጋርነት ስምምነት ትናንት ተፈራርሟል።

በወቅቱ እንደተገለጸው በመዲናዋ አገልግሎት እየሰጡ ባሉ ከ40 ሺህ በላይ የራይድ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ አሽከርካሪዎች አማካኝነት የቴሌ አገልግሎቶች እንዲቀርቡ ይደረጋል።

የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፍሬህይወት ታምሩ እንደገለጹት፤ በስምምነቱ መሠረት የራይድ ትራንስፖርት የአገልግሎት ክፍያዎችን በቴሌ ብር መፈጸም ይችላሉ።

በተጨማሪ የራይድ ትራንስፖርት የአገልግሎት ሰጪ አሽከርካሪዎች የተለያዩ የቴሌኮም አገልግሎቶችን በወኪልነት ወርሀዊ የአገልግሎት ክፍያዎችን ለመቀበል፣ አዲስ ደንበኞችን ለመመዝገብ፣ የደንበኞችን የቴሌብር ደንበኝነት ደረጃ ለማሳደግ፣ የአየር ሰዓትና የጥቅል አገልግሎቶችን ለመሸጥ ይችላሉ።

ከዚህ ባለፈ አሽከርካሪዎቹ በቴሌ ብር ገንዘብ የማውጣትና ማስገባት አገልግሎት፣ አዲስ ሲም ካርድ መሸጥ፣ ምትክ ሲም ካርዶችን ለደንበኞች ማድረስ፣ እንዲሁም በርካታ የተደራሽነት አገልግሎቶችን መስጠት እንደሚችሉ ገልጸዋል።

የኢትዮ ቴሌኮም ደንበኞች አገልግሎቱን ለማግኘት ከሚጠቀሙባቸው አማራጮች በተጨማሪ ወደ ራይድ አገልግሎት ማዕከል 8294 በመደወል፣ አገልግሎቱን ባሉበት ቦታ ሆነው ማግኘት እንደሚችሉም ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ አስታውቀዋል።

የሀይብሪድ ዲዛይንስ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሳምራዊት ፍቅሩ በበኩላቸው፤ ካምፓኒያቸው ከአንጋፋው



ፎቶ ኢዮብ ተፈራ

ኢትዮቴሌኮም ጋር በመስራቱ ዕድለኛ መሆኑን ጠቁመው፤ የራይድ አሽከርካሪዎች ደንበኞች ያሉበት ድረስ በመሄድ አገልግሎቱን ለመስጠት ቁርጠኛ መሆናቸውን ተናግረዋል።

የራይድ ትራንስፖርት አገልግሎት ተደራሽነቱን ወደ ሌሎች ከተሞች ሲያሳድግም የኢትዮ ቴሌኮም የደንበኞች አገልግሎቱም የራይድ ትራንስፖርት ተደራሽነት ባሉባቸው ከተሞች ሁሉ እንደሚሰጥም ገልጸዋል።

ኢትዮ ቴሌኮም የኅብረተሰቡን የተለያዩ የቴሌኮም ፍላጎቶችን ለማሟላትና ዘመኑ ያፈራቸውን አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመተግበር አኳያ በቀጣይነትም በአጋርነት ከሚሠሩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በትብብር እንደሚሠራ አሳውቋል።

የኢትዮ ቴሌኮም የቴሌ ብር አገልግሎት ተግባራዊ ከተደረገ ጀምሮ ለዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት መስፋፋት ጉልህ ሚና እየተጫወተ መሆኑን በስምምነቱ ወቅት ተጠቁሟል።

አገልግሎቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከ19 ነጥብ አራት ሚሊዮን በላይ ደንበኞች ያፈራና ከ82 በላይ ዋና ወኪሎች፣ ከ69ሺ. በላይ ወኪሎችና ከ18 ሺ. በላይ ነጋዴዎች ማፍራት እንደተቻለ ኢትዮ ቴሌኮም አስታውቆ፤ በዚህም ከ18 ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር በላይ የኤሌክትሮኒክስ ገንዘብ ዝውውር በቴሌብር መፈጸሙን ገልጿል።


ዶክተር እዮብ ተካልኝ

# ያልተጠናቀቁ የካፒታል ፕሮጀክቶች በ2015 በጀት ዓመት በአነስተኛ ወጪ ለአገልግሎት እንደሚበቁ ተገለጸ

አዲስ አበባ፡- በ2015 በጀት ዓመት አዳዲስ ካፒታል ፕሮጀክቶች ተግባራዊ እንደማይደረጉ እና ያልተጠናቀቁ የካፒታል ፕሮጀክቶችን በአነስተኛ ወጪ በትጋት በማጠናቀቅ ለአገልግሎት ለማብቃት ከፍተኛ ጥረት እንደሚደረግ የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር እዮብ ተካልኝ ገለጹ።

የ2015 በጀት አመት የፌዴራል መንግሥት በጀት ባነሰ ወጪ ብዙ ሥራ ለማከናወን በሚያስችል ጥብቅ የፊሲካል ፖሊሲ ማዕቀፍ በመመራት እየተዘጋጀ መሆኑንም የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታው ተናግረዋል።

የገንዘብ ሚኒስቴር የፖሊሲ ጉዳዮች ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር እዮብ ተካልኝ የ2015 በጀት አመት የበጀት ዝግጅትን አስመልክተው እንደገለጹት፣ 170 የፌዴራል ባለበጀት መስሪያ ቤቶች ከገንዘብ ሚኒስቴር በተሰጣቸው የበጀት ጣሪያ መሠረት ከሚያዝያ 25 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የ2015 በጀታቸውን ለሚኒስቴሩ አቅርበው ማስገምገማቸውን ጠቅሰዋል።

የ2015 በጀት በጥብቅ የፊሲካል ፖሊሲ ማዕቀፍና የአገሪቱን ማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ እየተዘጋጀ መሆኑን መናገራቸውን ከገንዘብ ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።

የበጀት ዝግጅቱ ስትራቴጂያዊ ለሆኑ የኢኮኖሚ ዘርፎች ማለትም ለግብርና፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለማዕድን፣ ለቱሪዝምና ለዲጂታል ቴክኖሎጂ ትኩረት የሚሰጥ መሆኑን ዶክተር እዮብ አመልክተው፣ በአንዳንድ ዘርፎች ላይ ደግሞ ከመደበኛ በጀት ላይ እስከ 40 በመቶ የሚሆን ቅናሽ እንደሚደረግ አብራርተዋል።

የበጀት ጉድለትን በተመለከተም ከውጭ የሚገኘው ሀብት በታሰበው መጠን ላይገኝ ስለሚችል መንግሥት ከአገር ውስጥ ከሚመነጨው ሀብት ማለትም ከግምጃ ቤት ሰነድና ከሌሎች የአገር ውስጥ ምንጮች ለማሟላት የአገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ነድፎ ተግባራዊ በማድረጉ አበረታች ውጤት በመገኘቱ የበጀት ጉድለቱ የዋጋ ግሽበትን በማያባብስ ሁኔታ ለማሟላት ጥረት ይደረጋልም ብለዋል።

በ2015 በጀት አመት አዳዲስ ካፒታል ፕሮጀክቶች ተግባራዊ እንደማይደረጉ ዶክተር እዮብ ጠቅሰው፣ ይልቅ ተጀምረው ያልተጠናቀቁ የካፒታል ፕሮጀክቶች በአነስተኛ ወጪ በትጋት በማጠናቀቅ ለአገልግሎት ለማብቃት እንዲቻል የፌዴራል ባለበጀት መስሪያ ቤቶች የ2015 በጀታቸውን ባስገመገሙበት ወቅት ጥብቅ መመሪያ እንደተሰጣቸውም አስረድተዋል።

የ2015 የፌዴራል መንግሥቱ በጀት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር በቤት ቀርቦና ውይይትና ክርክር ተደርጎበት ሲጸድቅ ከሐምሌ 1 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ እንደሚውል ይታወቃል።

# በደቡብ ክልል የተጀመረው ሕግ የማስከበር ተግባር ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተገለጸ

**መዓዛ ማሞ**

አዲስአበባ፡- በደቡብ ክልል የተጀመረው ሕግ የማስከበር ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የክልሉ የሰላም እና የጸጥታ ቢሮ ገለጸ።

በክልሉ በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የመልካም አስተዳደር ዘርፍ አስተባባሪና የሰላምና ጸጥታ ቢሮ ኃላፊ የሆኑት አቶ አለማየሁ ባዉዲ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በክልሉ አንዳንድ አካባቢዎች ከአደረጃጀት እና ከአስተዳደር ወሰን እና ከማንነት ጥያቄዎች ጋር ተያይዞ ችግሮች መፈጠራቸው የሚታወስ ነው። በኮንሶ እና አሌ አከባቢ፣ በኮንሶ ዞን ሰገን ዙሪያ ወረዳ አከባቢ፣ በደራሼ ልዩ ወረዳ እና በደቡብ ኦሞ ዞን አካባቢ የተፈጠሩ የጸጥታ ችግሮች ነበሩ።



**አቶ አለማየሁ ባዉዲ**

ግጭቶቹን ሕዝቡን በማይወክል መንገድ የተወሰኑ ቡድኖች ለግል ጥቅም ማስፈጸሚያ ለማድረግና ለማባባስ ሞክረው እንደነበረ የቢሮ ኃላፊው ተናግረው፣ የነበረውን ችግር በአግባቡ በመቆጣጠር ግጭት ጠንሳሾችን እና የግጭቱ ተሳታፊዎችን በሕግ ቁጥጥር ስር ማዋል እንደተቻለ ተናግረዋል።

አቶ አለማየሁ ባዉዲ እንደተናገሩት፣ በደራሼ አካባቢ «የዞን መዋቅር ሊፈቀድልን ይገባል» በሚል መንግሥት ካስቀመጠው አቅጣጫ ውጪ የተወሰኑ ቡድኖች ከሕዝቡ ጋር ስምምነት ላይ ከተደረሰበት መንገድ ውጪ በመነሳት ጉዳት አድርሰዋል። በዚህም የሕግ ማስከበር ሂደት ግጭቱን በበላይነት ሲመሩ የነበሩ እና በጥፋት ሥራው ላይ የተሳተፉ ከ400 በላይ ሰዎች በሕግ ቁጥጥር ስር መዋላቸውን ተናግረዋል።

በደራሼ አካባቢ በሕግ ማስከበር ላይ በልዩ ሁኔታ መሠራት ያለበት ሥራ በመኖሩ የፌዴራል ተቋማት እገዛ በማድረግ ተለይቶ ኮማንድ ፖስት በማቋቋም እየተመራ ሥራዎች ተጠናክረው እየተሠሩ እንደሆነ ጠቁመዋል።

በደቡብ ኦሞ ዞንም ከአሪ የዞን ጥያቄ ጋር ተያይዞ አንዳንድ ኃይሎች ጥያቄውን በኃይል ለማስፈጸም ንብረት አውድመዋል፤ ሰዎች አፈናቅለዋል። ችግሩ ሳይሰፋ መቆጣጠር መቻሉን የተናገሩት የቢሮ ኃላፊው ሕዝቡን የማይወክሉ አጥፊዎች ተይዘው ሕግ መከበር ስላለበት ግጭቱን የመሩ እና የተሳተፉ ከ600 በላይ ሰዎች እንደተያዙ ተናግረዋል። የተፈናቀሉ ዜጎችን የማስመለስ፣ የምርመራ ሥራ እና ሌሎች ሕግ የማስከበር ሥራዎች በተቀናጀ መልኩ ተጠናክረው እንደሚቀጥሉም አያይዘው ገልጸዋል።

የቢሮ ኃላፊው እንደተናገሩት፣ አሌ እና ኮንሶ አካባቢ በአስተዳደር ወሰን ምክንያት የነበሩ ግጭቶችን በመፍታት መንግሥት ኃላፊነቱን ወስዶ እየሠራ ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ የክልሉ መንግሥት አቅዶ እየሠራ ያለው ጉዳይ መልክ እንዳይዝ የሚፈልጉ የፖለቲካ ነጋዴዎች ግጭቱ እንዲባባስ ሠርተዋል። በአካባቢው የነበረውን ግጭት በመቆጣጠር በዚህ ተግባር የተሳተፉ አመራሮችን ጨምሮ እርምጃ በመውሰድ በሕግ ቁጥጥር ስር ውለዋል። በዘላቂነት መፍትሄ የሚሰጠው የተጀመረውን ሥራ የአስተዳደር ወሰን ማካለል፣ ውስጥ ለውስጥ ሴራ እያሴሩ ያሉትን አካላት ማጋለጥ እና ሕዝቡ ትናንት የነበረውን አብሮነት እንዲያጠናክር የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ስልጤ ዞን አካባቢ ከሃይማኖት ጋር ተያይዞ ተከስቶ የነበረው ነገር ግጭቱን የክርስቲያን እና የሙስሊም ግጭት ለማድረግ ቢሞከርም በአግባቡ በመቆጣጠር በቤተ እምነቶች ሽፋን የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች በቁጥጥር ስር እንደዋሉ እና የምርመራ ሥራው ተጠናክሮ እንደቀጠለ ተናግረዋል።

የቢሮ ኃላፊው እንደሚሉት የአሸባሪው ሸኔ እንቅስቃሴ በክልሉ አዋሳኝ አካባቢዎች ይስተዋላል። በጌዲዮ ዞን፣ በአማሮ ልዩ ወረዳ፣ በቡርጂ ልዩ ወረዳ፣ ኮንሶ ጥግ እና ደቡብ ኦሞ አካባቢም አጋጣሚዎችን ሲያገኝ ሰዎችን የመግደል፣ ትንኮሳዎች፣ ዝርፊያ እና ንጥቂያዎች ያካሂዳል። እንቅስቃሴውን ለመቆጣጠር እና የሕዝቦች አብሮ የመኖር እና የክልሎች የእርስ በእርስ ግንኙነት እንዳይበላሽ የተደራጀ ሥራ እየተሠራ ነው። በፌዴራል ደረጃም የፌዴራል ፖሊስ ከክልሉ የጸጥታ ኃይል ጋር ተቀናጅቶ የሸኔን እንቅስቃሴ ለመግታት የተጀመሩ ሥራዎች እንዳሉ አመላክተዋል።

በአብዛኛው የአማሮ እና ቡርጂ መንገድ የሸኔ ቡድን የሚንቀሳቀስባቸው ቀጣናዎችን አቋርጦ የሚሄድ በመሆኑና በተበታተነ መንገድ ጥቃት ስለሚያደርሱ መንገዶች ለረዥም ጊዜ ተዘግተው መቆየታቸውን ተናግረው አሁንም አስተማማኝ አለመሆኑን ተናግረዋል። ገና ብዙ ሥራ የሚጠይቅ እና ከሁለቱ ክልሎች አቅም በላይ የሆኑ ቦታዎች እንዳሉ በመተማመን የፌዴራል ተቋማት እንዲረከቡት በማድረግ የኦፕሬሽን ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል።

አቶ አለማየሁ ባዉዲ አክለውም ሕዝቡ መንግሥት በሚያደርገው ሕግ የማስከበር እንቅስቃሴ ውስጥ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ጥሪ አቅርበዋል።

# የሕወሓት ቡድን የሥልጣን ዘመኑን ለማራዘም አሁንም ሕዝቡን ለማሳሳት እየሞከረ ነው

**መአረግ ገ/እግዚአብሔር**

አዲስ አበባ፡- የሕወሓት ቡድን የሥልጣን ዘመኑን ለማራዘም ሕዝቡን ለማሳሳት እየሞከረ ነው ሲሉ የቀድሞ የሽሬ እንዳስላሴ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ኢንጂነር የማነ ኃይሌ ተናገሩ።

ኢንጅነር የማነ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ለሚታተመው ለወጋህታ ጋዜጣ እንደተናገሩት፣ ሕወሓት የትግራይን ሕዝብ በውሸት ፕሮፓጋንዳ በማታለል ወደ ጦርነት እንዲገባ አድርጓል። በዚህም ሕዝቡ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበታል።

እንደ ኢንጅነር የማነ ገለፃ፣ ሕወሓት አሁንም የራሱን ሥልጣን ለማራዘም የትግራይን ሕዝብ እያደናገረ ወደ ጦርነት ለማስገባት እየሞከረ ነው የሚገኘው፤ ለራሱ ብቻ እንጂ ለትግራይ ሕዝብ አያስብም። በዚህ ቡድን ምክንያት ከዚህ በፊትም ቢሆን በድህነት እና በስቃይ ውስጥ ወድቆ የነበረ ሕዝብ ነው።

ሕወሓት ሕዝቡን እያሳሳተ ወደ ጦርነት የሚያስገባበት ምክንያት ከዚህ ቀደም ጭምር በትግራይ ሕዝብ ላይ ለፈጸመው ወንጀል ተጠያቂ ላለመሆን ነው።

እንዲሁም አዲስ ጦርነት በመክፈት ወጣቱን አስገድዶ ወደ ጦርነት በመክተት በሥልጣን ላይ ለመቆየት መሆኑንም አክለዋል።

ቡድኑ ለሥልጣኑ ብቻ የሚያስብ እንጂ ካለፈው ስህተቱ የሚማር አይደለም ያሉት ኢንጅነር የማነ፣ የራሱን መጥፎ አጀንዳ ለማሳካት ሲል የትግራይን ሕዝብ ከሁሉም አጎራባች ሕዝቦች ጋር በማጣላት ችግር ውስጥ ከቶታል።

ይሁን እንጂ የትግራይ ሕዝብ በአሁኑ ሰዓት የሕወሓትን መጥፎ አጀንዳ በመረዳት ወደ ተለያዩ አጎራባች ክልሎች እየሄደ ነው።

በዚህ ቡድን ምክንያት የትግራይ ሕዝብ ከፍተኛ ስቃይ ደርሶበታል። ቡድኑ ሕዝቡን በማታለልና በማስገደድ ወደ ጦርነት መከተት ሥራው እንደሆነና



**ኢንጂነር የማነ ኃይሌ**

ሕዝቡ ግን ተገድዶ ካልሆነ በስተቀር የጦርነት ጥሪውን እንደማይቀበለው ኢንጂነር የማነ ኃይሌ ተናግረዋል።

የትግራይ ሕዝብ በቡድኑ ምክንያት ያልደረሰበት መከራና ስቃይ የለም ያሉት ኢንጅነር የማነ ብዙ ወጣቶች ተሰውተዋል፤ የአካል ጉዳተኞችም ሆነዋል ሲሉ ተናግረዋል።

ሕወሓት አሁንም እንደ አዲስ የጦር ነጋሪት መጎሰም የትግራይ ወጣቶችን ለማስጨረሽ ካልሆነ በስተቀር በቀደሙት ጦርነቶች ያልተሳካለት ከዚህ በኋላ ይሳካለታል ተብሎ እንደማይጠበቅ ገልጸዋል።

ሕዝቡ በሕወሓት ምክንያት እልቂት እየደረሰበት መታገስ የለበትም፤ ጥያቄ ማንሳት አለበት። «ልጆቻችንን ለተጨማሪ ጥፋት አንሰጥም በማለት በውጭም ሆነ በውስጥም ያሉ የትግራይ ተወላጆች መጠየቅ እና አመጽ ማንሳት አለባቸው» ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# መከላከያ የኢትዮጵያን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ማንኛውንም አካል የመመከትና አስፈላጊውን ዕርምጃ የመውሰድ ብቃት አለው ሲሉ ተናግረዋል።

የመከላከያ ሰራዊት ኢትዮጵያን ለመበተን የተነሱ ክፉዎችን ህልም ያከሸፈ የቁርጥ ቀን ልጅ እንደሆነም አንስተዋል።

መከላከያ የታጠቃቸውን የውጊያ መሣሪያዎች፣ ተሸከርካሪዎችን እና የሰራዊቱን የማድረግ አቅም በየጊዜው በማረጋገጥ ከውስጥም ይሁን ከውጭ በአገራችን ሉዓላዊነት ላይ የሚቃጣውን ጥቃት መመከት የሚያስችል ዝግጁነት አለው ብለዋል።

የሰራዊቱ አመራርና አባላት እራሳቸውን በየወቅቱ እያጠናከሩ ከምንም ጊዜ በላይ ዝግጁነታቸውን እያረጋገጡ መሆኑን ገልጸዋል።

22ኛ ንስር ክፍለ ጦርም በርካታ ድሎችን በተለያዩ አውደውጊያዎች መፈፀሙን ጠቁመው፤ መላ ኢትዮጵያውያን እንደ ልጃቸው የሚያዩት፣ እንደ አይናቸው ብሌን የሚጠብቁት፣ ሁሉም እናቶች መቀነታቸውን የፈቱለት ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ አሁን ለደረሰበት ደረጃ የደረሰው በዚህ ክፍለ ጦር የማይለካ ሚና ነውም ብለዋል።

ክፍለ-ጦሩ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ለአፍታም ቢሆን እንዳይደናቀፍ መስዋዕትነት እየከፈለ የሚገኝ ነው ሲሉ ገልጸውታል።

የምዕራብ እዝ ዋና አዛዥ ሌተናንት ጄነራል መሠለ መሠረት በበኩላቸው፤ 22ኛ ንስር ክፍለ ጦር በርካታ ጀግኖችን ያፈራች ፣ ለበርካታ ጀግና ክፍለጦሮች መፈልፈያ መሆኗን ገልፀዋል።

ክፍለ ጦሯ በአሁኑ ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ትመራ የነበረች ክፍለ ጦር እንደነበረች አስታውሰው፤ ዛሬ ላይ እሳቸው በተገኙበት የሽልማትና የእውቅና ፕሮግራም በመድረሳችሁ እንኳን ደስ አላችሁ ኩራት ሊሰማችሁ ይገባል ብለዋል።

የኢፌዴሪ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ በክፍለ-ጦሩ ለሚገነባው የጀግኖች ሰማዕታት መታሰቢያ ሐውልት የመሠረት ድንጋይ አስቀምጠዋል። አመራሮቹ በክፍለ-ጦሩ ግቢ ውስጥ የችግኝ ተከላም አካሂደዋል።

በመርሃ-ግብሩ ላይ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ርዕሰ-መስተዳድር አቶ አሻድሊ ሀሰንን፣ የ22ኛ ንስር ክፍለ ጦር አዛዥ ብርጋዴር ጀኔራል ሰይፈ ኢንጌ እና ሌሎች ከፍተኛ አመራሮች ተገኝተዋል።

# ‹‹የኢትዮጵያ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ግንኙነታችን እንዲሁም ለአህጉራዊ ትብብር ወሳኝ ነው» ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፕሬዚዳንት ሞሐመዱ ቡሃሪ ለተደረገላቸው ደማቅ አቀባበልም ምስጋና አቅርበዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከናይጄሪያ ቆይታ በኋላ ወደኢኳቶሪያል ጊኒ አምርተዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ማላቦ ሲደርሱ በአገሪቱ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ደማቅ አቀባበል ተደርጎላቸዋል።

ዶክተር ዐቢይ በማላቦ ቆይታቸውም በሰብዓዊ እርዳታ፣ ፀረ ሽብር ጉዳዮች ላይ እና ኢ-ሕገመንግሥታዊ በሆነ መንገድ ሥልጣን ለመያዝ የሚደረጉ ጥረቶችን መከላከል ላይ በሚያተኩረው በኅብረቱ ጉባኤ ላይ ይሳተፋሉ ተብሎ ይጠበቃል።

የኅብረቱ ልዩ የመሪዎች ጉባኤ ዛሬና ነገ እንደሚከናወን ከተያዘለት መርሃግብር መረዳት ተችሏል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሰብዓዊ ድጋፉ በችግር ውስጥ ላለው የትግራይ ሕዝብ እየደረሰ ስለመሆኑ ሊፈተሽ ይገባል!

አሸባሪው ሕወሓት በሀገር ላይ በፈጸመው ክህደት ሀገራችን ወደማትፈልገው ጦርነት ገብታ እንደቆየች ይታወሳል። በውስጥም በውጭም የኢትዮጵያን መበታተን የሚፈልጉ ኃይሎች እና ተላላኪዎች ለእኩይ ተግባራቸው አንድነታቸውን አጠንክረው ሲታገሉ ቆይተዋል።

ሀገር ለማፍረስ ከላይ ታች ሲሉ ከርመዋል። በሂደቱም ሀገራችንና ሕዝቧ ለተለያዩ ችግሮች ተዳርገዋል። በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ዙሪያ በርካታ መመሰቃቀሎችም አጋጥመዋል። ብዙዎች በሚያውቁትም ሆነ በማያውቁት ተሰውተዋል። ንብረቶች ወድመዋል። ዜጎች አሰቃቂ የሚባሉ ጉዳቶችን ሁሉ አስተናግደዋል፤ ከቀያቸው ተፈናቅለዋል። በአጠቃላይ በሀገር ላይ የደረሰው ሰብአዊ ቀውስ ቀላል የሚባል አይደለም።

ይሁን እንጂ የሀገርን ህልውና የማስከበር ኃላፊነት ያለበት መንግሥት ከመላ ኢትዮጵያውያን ጋር ተባብሮ በአንድነትና በአንድ መንፈስ በከፈሉት መስዋዕትነት የተጠነሰሰውን ሴራ ሁሉ አምክነዋል። ያም ሆኖ አሸባሪው ሕወሓት በአልሸነፍም ባይነት ግትር አቋሙ ሳይረታ ለዳግም ጦርነት ያለ የሌለ ኃይሉን አደራጅቶ ለሁለተኛ ዙር ዳግም ወረራ ፈጽሟል።

ይሄም ቢሆን በጠንካራው ሕዝብ አንድነት እና በመንግሥት ቆራጥ አመራርነትና ግንባር ቀደም አመራር በኢትዮጵያውያን አሸናፊነት ተጠናቋል። በዚህም የትግራይ ሕዝብ ሳያውቅ ከገባበት ልጆቹን በጦርነት ከገበረበት እና አሁን ሊገብር እየተዘጋጀ ካለበት ጦርነት አረፍ ብሎ ወደ ልማት እንዲገባ፤ የማሰቢያ ጊዜ ተሰጥቶታል።

ሆኖም ግን አሸባሪው ቡድን አሁንም ከሽንፈቱ ሳይማር ፣ ከጥፋቱ ሳይጸጸት ለሦስተኛ ዙር ጦርነት ነጋሪት እየጎሰመ ይገኛል። አሁንም ለሰብአዊ እርዳታ የሚገባን ምግብ፣ መድኃኒትና ሌሎችንም ድጋፎች ለተራበውና ለተቸገረው የትግራይ ህዝብ ከማቅረብ ይልቅ ለጦርነቱ ለሚያሰለጥናቸው እንዲሁም ላሰበው ቀጣይ ጦርነት ስንቅ በማዘጋጀት ላይ ነው።

ይሄንንም እውነታ ከአሸባሪ ቡድኑ በተለያየ መልኩ አምልጠው የመጡና አልፎ አልፎም የቡድኑ ከፍተኛ አመራሮች ጭምር እንደ ጀብዱ ሲደሰኩሩ ተደምጠዋል። የሰብአዊ ርዳታ ይዘው የሄዱ መኪኖች ተጨማሪ ሰብአዊ ርዳታ እንዳያጓጉዙ የሽብር ቡድኑ ለጦርነት ዓላማው ማስፈጸሚያ አውሎታል።

ይሄንንም በተለያየ መልኩ ማየትና ማረጋገጥ ተችሏል። አሁንም በምርኮኝነት ይዟቸው የነበሩትን ንጹሀን ዜጎች ያስወጣውም በእነዚሁ የዓለምአቀፍ ርዳታ ድርጅቶች ሰብአዊ ምግብና መድኃኒት በወሰዱ መኪኖች መሆኑም መኪኖቹን ለሽብር ተግባር እያዋላቸው መሆኑ ከሚወጡ መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል።

አሁንም መንግሥት የትግራይን ህዝብ ለመታደግ ለሰብአዊ ርዳታ ማስገቢያ ኮሪደር በመፍቀድ የሰብአዊ ርዳታ በብዛት ወደ ትግራይ እንዲገባ አድርጓል። በዚሁም መሰረት በርካታ ቁጥር ያለው ሰብአዊ ርዳታ የጫኑ ተሽከርካሪዎች ወደ መቐለ ገብተዋል። ሰሞኑንም ለአምስተኛ ዙር መቐለ የገቡት የቀይ መስቀል ኮሚቴ ተሽከርካሪዎች የህክምና ቁሳቁስ፣ የምግብ ድጋፎችን፣ የውሃ ማጣሪያ ግብዓቶችን እና አስፈላጊ የቤት ቁሳቁስ የያዙ ናቸው።

ምንም እንኳን ድጋፉ በዚህ መልኩ ወደክልሉ ቢገባም አሸባሪው የሕወሓት ቡድን ሰብአዊ ርዳታና መድኃኒት ለተገቢው ህዝብ እንዲደርስ እያደረገ አይደለም። ህጻናት እየተራቡ የሚያጠቡ እናቶች እና አረጋውያን እንደ እንጨት ደርቀው ባሉበት ሁኔታ የሰብአዊ ርዳታውን ለጦርነቱ ዓላማ ግብአትነት እያዋለው ይገኛል።

በእርግጥ አሸባሪው ሕወሓት ከትግል ወቅት ምስረታው ጀምሮ የሚታወቀው የትግራይን ህዝብ ሲጠቅም ሳይሆን ለህዝቡ ታስቦ የመጣን ሰብአዊ ርዳታ ሸጦ ለጦርነት ማካሄጃ የጦር መሳሪያ ሲገዛበት ነው። አሁንም በነበረው ጦርነት የህጻናትን አልሚ ምግብ ሳይቀር ያዋለው ለጦርነቱ ላሰለፋቸው ተዋጊዎች እንጂ ለተራቡና ለተቸገሩ ህጻናት አይደለም። ይሄንንም ሆነ የነበረ ታሪኩን የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ጠንቅቆ ያውቀዋል። ስለሆነም ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ሰብአዊ ርዳታውን መስጠትና ወደ ትግራይ እንዲጓጓዝ ማድረግ ብቻ ሳይሆን በትክክለኛው መንገድ ለተረጂው ማህበረሰብ መድረሱን ማረጋገጥ አለበት።

በትክክል ለተራበው የትግራይ ህዝብ መድረሱን መከታተል አለበት። የመንግሥት ድርሻ ለሰብአዊ ርዳታ ኮሪደር መክፈት ነው። ይሄ ደግሞ በሚገባ ሆኗል። ስለዚህ ቀሪውና ሰብአዊ ርዳታው ለህዝቡ እንዲደርስ የማድረጉ ሥራ የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ጉዳይ መሆን አለበት።

ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ይሄን የሕዝብ ቅሬታ እያደመጠ ለምን ዝም አለ? የሰብአዊ ርዳታ የጫኑና የገቡ መኪኖች ሳይመለሱ ለጦርነት ተግባር አገልግሎት ላይ እየዋሉ ነው ሲባልስ ለምን ዝምታን መረጠ? የሚለው ግን ትልቅ ጥያቄ የሚያስነሳ ጉዳይ ነው። አሁንም ቢሆን ዓለምአቀፉ ማህበረሰብ ይሄንን ዝምታ ሰብሮ ለተቸገረው የትግራይ ህዝብ የሰብአዊ ድጋፉ እየደረሰው ስለመሆኑ ክትትል ሊያደርግ ይገባል!


ኢፕድ

**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## ለሁሉም ነገር ልክ አለውና ሕጋዊ ዕርምጃ ተገቢ ነው!

**በእምነት**

ቃልና ተግባር አልገናኝ እያለ እንጂ ስለሰላም ያልተባለ ያልተነገረ ኺረ እንደውም ያልተሞከረ ነገር የለም።የሃይማኖት አባቶች ፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ምሁራን፣ ፖለቲከኞችና የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ስለሰላም ብዙ ብለዋል፡፡

እንደ እኔ እይታ አሁን አሁን ግልጽ እየሆነ የመጣው ነገር የሰላም መደፍረሱ ችግር ያለው ሕዝቡ ውስጥ ሳይሆን፣ ሥልጣንን በአቋራጭ ለማግኘት የሚፈልጉ ኃይሎች ዘንድ መሆኑ ነው።ለሕዝብ ሕይወትና አካላዊ ደኅንነት ደንታ የማይሰጣቸው የግል ጥቅማቸውን ስልጣን ላይ ሆነው ፈላጭ ቆራጭ መሆን ህልማቸው የሆኑ ወገኖች ሰላም እያደፈረሱ ሀገርን ቀውስ ውስጥ በመክተት፣ የሚመኙትን ሥልጣን ለመቆጣጠር ምንም ነገር ከማድረግ እንደማይመለሱ በግልጽ እያሳዩ ነው፡፡

ሥልጣን በሕዝብ ፈቃድ የሚገኝ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አንዱ መደላድል መሆኑ ቢታወቅም፤ እነዚህ ሃይሎች ግን ከዚህ በተቃራኒ በሕገወጥ መንገድ በመንቀሳቀስና የህዝቡን ሰላም በማወክ ወጥቶ መግባት ሰርቶ ቤተሰቡንና ራሱን ማስተዳደር ላይ ችግር እየፈጠሩ በጠቅላላው ሰላሙን እያደፈረሱ ነው፡፡

እዚህ ላይ በመንግሥት ወገንም ሆነ በህዝቡ ዘንድ ቆመናል የሚሉ በአደባባይ ስለሰላም የሚሰብኩ ወገኖችም ቢሆኑ ደፈር ብለው አጥፊውን በማውገዝ መስመር ማስያዝ ላይ ከፍተኛ ክፍተት ይስተዋላል።ምክንያቱምም ሕግን በማስከበርና የሕዝቡን ሰላም ከማረጋገጥ አኳያ የኋሊት ከመሄድ ተላቀውና ከታይታ የዘለለ ተግባር አከናውነው ማሳየት እያቃታቸው ቃል ብቻ እየሆኑ ነው።በዚህ ሁኔታ መቀጠል እንደማይቻል ግን የሁሉም ልቦና ያውቀዋል።ሰላምን መስበክ አስፈላጊ ቢሆንም ተግባር ግን መተኪያ የሌለው ነገር መሆኑም ሊታወቅ ይገባል፡፡

ሰዎች ከፍርሃት፣ ከጥላቻ፣ ከግጭትና ከውድመት ተጠብቀው በነፃነት የሚኖሩበት ድባብ መገለጫው ሰላም ነው፤ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ መስኮች ደግሞ አገርን ለማሳደግ የሚረዳ መሣሪያም ስለመሆኑ ምንም የሚያጠያይቅ አይደለም ።ኢትዮጵያ ውስጥ በጠቅላይ ሚኒስትር አቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የሚመራው አስተዳደር በይፋ ሥራ ከጀመረበት ከመጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም ወዲህ በርካታ አዎንታዊና ተስፋ ሰጪ ጅምሮች ቢታዩም፣ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ባጋጠሙ ግጭቶች ምክንያት በርካቶች ህይወታቸውን አጥተዋል እያጡም ነው፣ ለአካላዊና ሥነ ልቦናዊ ጉዳት የተዳረጉም በርካታ ናቸው፣ ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ ዜጎችም ቁጥር ቀላል አይደለም ፡፡

ምንም እንኳን ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጨምሮ ብዙሃኑ ስለሰላም በተደጋጋሚ ብዙ ነገር ቢሉም ፣ በየቦታው ግጭቶች እያገረሸ የሀገር ሰላም ደፍርሷል።በሕዝቦች መካከል ምንም ዓይነት ችግር ሳይፈጠር፣ የግጭት ነጋዴዎች በሚቀሰቅሱት ሁከትና ውዥንብር ምክንያት በርካቶች የሰላም ያለህ ለማለትም ተገድደዋል።ስለሰላም አስፈላጊነት ብሎም የህግ የበላይነትን ስለማስከበር ብዙ ቃል በተደጋጋሚ ቢሰማም ተግባር ግን ጠፍቷል፡፡

አንዳንድ ጊዜ የሚታዩ በተለይም ደግሞ ከቃል የማይዘሉ የህግ እናስከብራለን ዘመቻዎች ተደጋግመው ሲሰሙ ለእኔ የሚፈጥርብኝ ነገር መንግሥት ሕግ ማስከበር ከምንም በላይ ተቀዳሚ ኃላፊነቱ መሆኑ ስለመርሳቱ ነው። አዎ አሁንም ቢሆን በሀገር አቀፍ ደረጃ በተለያዩ አካባቢዎች የሚስተዋሉ ግጭትና አለመረጋጋቶች መፍትሔ እንዲያገኙ ከልብ የሚፈለግ ከሆነ በብዙ ሥፍራዎች ላይ ያሉ የአስተዳደርና የፀጥታ መዋቅሮች ሥራቸውን በአግባቡ ሊያከናውኑ ግድ ይላቸዋል።የሕግ የበላይነት ሲጠፋ ሥርዓት አልበኝነት መስፈኑ አይቀሬ ነው።ስርዓት አልበኝነት ተንሰራፋ ማለት ደግሞ እንደ ሀገርና ህዝብ የመቀጠላችን ነገር ጥያቄ ምልክት ውስጥ ወደቀ ማለት ነው፡፡

መንግሥት የሕዝብን ደህንነት ማስከበር ሲያቅተውና ሕገወጦች የበላይነቱን ሲይዙ ቀውስ ይፈጠራል።ቀውሱን የሚፈልጉ አካላት አጋጣሚውን በመጠቀም በእሳት ላይ ቤንዚን እያርከፈከፉ እሳቱን ቁጭ ብለው ይሞቁታል።እየሆነ ያለውም ይኸው ነው።የፌዴራል መንግሥትና የክልል ብሔራዊ መንግሥታት እየተናበቡ የሰላምን የጸጥታ እንዲሁም ህግን የማስከበር ስራን ካልሰሩ እንኳንስ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ለማምራት ይቅርና ከቀውስ ውስጥ መውጣት ህልም ነው የሚሆንብን።ስለዚህ መንግሥት የዜጎችን መብት እያከበረና ሕጋዊ አካሄዶችን አሚጦ እየተጠቀመ ሕግ ማስከበር አለበት እላለሁ፡፡

ከሕጋዊነት በሚያፈነግጡት እንዲሁም ሕገወጥነትን የሚያቀነቅኑ ኃይላት ላይም በሕግ ልክ የማስገባት ኃላፊነት እንዳለበት መዘንጋት የለበትም። ኢትዮጵያውያን በገዛ ሀገራቸው በነፃነት መንቀሳቀስ ሲያቅታቸው መንግሥት እጁን አጣጥፎ የሚያያቸው ከሆነ ዋል አደር ሲል ዳፋው ለእሱም እንደሚተርፍ መገንዘብም ያስፈልጋል። ለሁሉም ነገር ልክ አለውና ሕጋዊ ዕርምጃ ተገቢ ነው።ከዚህ ውጪ ስለሰላም መለፈፍ ፋይዳ ቢስ ይሆናል፡፡

መንግሥት ፍትህን በማስፈን አጥፊዎችን መቅጣቱ ለሌሎች ማስተማሪያ ከመሆኑም በላይ የመንግሥትነት ኃላፊነቱንም የመ ወጫው አንዱ ምልክት ተደርጎ የሚወሰድ ነው። በመሆኑም ሀገሪቱን በማስተዳደር ላይ ያለው መንግሥት ህግና ስርዓትን የማስፈን ኃላፊነቱን በአግባቡ፣ በተገቢው ሁኔታ፣ ጊዜና ቦታ በትልቅ ቁርጠኝነት ሊያሰፍን ይገባል። እኛም እንደ ዜጋ ከዚህ ህግና ስርዓትን ከማስፈን ስራ ጎን በመቆም አጥፊዎችን በመገሰጽ፣ አልፎም ለመንግሥት ተላልፈው የሚሰጡበትን ሁኔታ በቆራጥነት በመስራት አጋርነታችንን ማረጋገጥ ይኖርብናል።

ይህንን ሳናደርግ ግን በሰላም ወጥተን መግባት የምንችገር ብቻም ሳይሆን፤ እዚህም እዚያም የሚሰሙ የሰላም መደፍረሶች አሳሰቡን ከመናገር ባለፈ ዝምታን ከመረጥንና ለአንድ ወገን ብቻ የምንተው ከሆንን ሰላምን የማስፈንና ሕግን የማስከበር ርምጃዎች ሁሉ በአንድ እጅ እንደማጨብጨብ ነው የሚቆጠረው። በመሆኑም ለሁሉም ነገር ልክ እንዳለው ስንናገር እና ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት ከቃል በላይ በተግባር ሊገለጽ እንደሚገባው ስንናገር፤ ከእኛ ምን ይጠበቃል ብለን የድርሻችንን በመወጣት ተግባራዊ እገዛ በማድረግ ሊሆን ይገባል!።አበቃሁ። ሰላም!

# ከግጭት ለማትረፍ ዘወትር የተዘረጉት የሕወሓት የሸብር እጆች

ማሙሻ ከአቡርሻ

ግባችንን ሰላም እና ዴሞክራሲ አድርገን ስንነሳ፤ መንገዳችን ሰላማዊ፣ አካሄዳችን ዴሞክራሲያዊ ይሆናል። መዳረሻችን ሁሉን አቀፍ ነጻነት ሆኖ ስንነሳ፤ መንገዳችን የሃሳብ ልዕልና የሚናኝበት የአዋቂዎች መተላለፊያ ይሆናል። የጉዟችን ፍጻሜ ሁሉን አቀፍ ከሆነ ብልጽግና ከፍታ ላይ ማረፍ ከሆነም፤ ርምጃችን በጥንቃቄና በማስተዋል የተሞላ፣ አካሄዳችንም ጅምሮችን በማፍረስ ሳይሆን መሰረቱን እያጸኑ ከፍ አድርጎ መገንባት ላይ ያተኮረ ይሆናል። እነዚህ ሁሉ ግን መነሻችን እውነት፤ ምልከታችን አገርና ሕዝብ፤ ማረፊያችን ከፍታ ሲሆን ብቻ የሚገለጡ ሃቆች ናቸው። ከዚህ በተቃራኒው ሲሆን ግን ከሀገርና ሕዝብ ይልቅ ቡድንና ግለሰብ ይነግሳሉ፤ ከእውነትና ሰላም ይልቅ ቅጥፈትና ሴራ ይገዝፋሉ።

በዚህ ረገድ ተነጋግሮ ከመግባባት ይልቅ ነፍጥ አንግቶ መሸፈትን፤ ከሰላም ይልቅ ኹከትን፤ ከወንድማማችነትና አብሮነት ይልቅ የመሳሪያ ምላጭ ስቦ መግደል መገዳደልን፤... ምርጫው አድርጎ ጫካ የገባው የሕወሓት ቡድን፤ በ17 ዓመታት የሽፍትነት ጉዞው አያሌ ግፎች፣ ጭፍጨፋና አሰቃቂ የግጭት አውዶችን ፈጥሮ ብዙዎችን ለመከራ ዳርጓል። ከደደቢት በረሃ እስከ መሃል ሸዋ አዲስ አበባ እልፍ በደሎችን እየፈጸመ፣ የበዙ የሰብዓዊ ቀውሶችን እያስከተለ፣ ለትውልድ ከፉ አሻራን ያኖሩ የጥፋት መንገዶችን መርጦ ተጉዟል።

ከ17 ዓመታት የግጭት፣ የውድመትና የጥፋት ጉዞው ማግስት በውጪው ኃይል ድጋፍና እገዛ ላይ ተንጠልጥሎ ለመንግሥትነት የበቃው ይህ የሕወሓት የጥፋት ቡድን፤ የሚመራትን ሀገር ሳይወድ፣ የሚመራውን ሕዝብ ሳያከብር 27 ዓመታትን በሥልጣን ላይ ቆየ። እነዚህ 27 ዓመታት የሥልጣን ዘመኑ ግን በሽምቅም፣ በግንባርም ሲፈጽመው ከቆየባቸው የ17 ዓመታት የጫካ ሕይወቱ የከፉ የሴራ እና የሰብዓዊ ቀውስ ዓመታት ሆነው ያለፉ ነበሩ። ምክንያቱም ሀገር ሳያውቅ ሀገር እንዲያፈርስ በውጪ ኃይሎች ድጋፍ ለስልጣን የበቃ ቡድን ዓላማውም ግቡም ሀገር ማፍረስ ስለነበር ሀገር ለማፍረስ ያስችሉኛል ያላቸውን የጋላቢዎቹን የቀደመ ሴራ ወደመተግበር ገባ።

ለዚህ ደግሞ ቀድሞ ሀገራዊ ስሜትን ማጥፋትና የብሔር ማንነትን ማግነን ዋናው ሥራ አደረገ። ይሄ በፈጠነ መልኩ እንዲጓዝለትም በሕዝቦች መካከል የኖረው አብሮነትና ወንድማማችነት በቂምና ቁርሾ እንዲተካ የሚያስችለውን ተረክ ከፍ አድርጎ ማስረጽ፤ አብሮነትና ወንድማማችነት በመጠራጠርና በመገፋፋት እንዲተካ ክፉ ዘር መዝራት የሥራው ሁሉ ቀዳሚ ሆነ። ይሄን የተቀበሉ ወዳጅ፤ ይሄን እንቢኝ ብለው የቀደመ አንድነትና ወንድማማችነትን እናጽና ያሉ "የቀድሞ ሥርዓት ናፋቂ፣ ጽንፈኛ፣ አሸባሪ፣ ትምክህተኛ፣ ጠባብ፣..." በሚል ተቀጽላ መሳደድ፣ መታሰር፣ መንገላታት፣ መፈናቀል፣ መገደል፣... እጣ ፈንታቸው ሆነ።

ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን አንዴ በብሔር፤ ሌላ ጊዜ በሃይማኖት ካባ በተሸሞነሞኑ ሴራዎች እዚህም እዚያም ግጭቶች እንዲፈጠሩ በማድረግ በሕዝቦች ግጭት የራስ ፍላጎትን የማሳካት መንግሥታዊ አቅሙን ለጥሩ ትወና ተጠቀመበት። አማራውን ከኦሮሞ፣ ጉራጌውን ከስልጤ፣ ሲዳማውን ከወላይታ፣ አፋሩን ከሶማሌ፤... እርስ በእርሱ እንዳይተማመን እና እንዲጋጭ አደረገው። ጨርሶ እንዳይጣላም የመንግሥትነት በትሩን ተጠቅሞ የሰላም ማስከበር ጣልቃ ገብነትን ይተገብራል። ይሄ የብሔር ቅብ ግጭት ፋታ ሲያገኝ፣ ነገር ግን የሰላም ነፋስ ሳይነፍስና ሕዝቡ ለምን ብሎ መጠየቅ ሳይጀምር ሌላ የብሔር ወይም የሃይማኖት ጥግ ይዞ ግጭት የሚፈጥር ክብሪት ይጭራል። ይሄም ገፍቶ ወደለየለት ግጭት ሳያመራ የተለመደው የአስታራቂነት ድራማው ይቀጥልና፤ ይሄን ችግር ማርገቢያ በሚል የሀብት ማሰባሰብ ይከወናል። እግረ መንገድም የሚፈለጉ ተቀናቃኝ ግለሰቦችና ቡድኖች እየተለቀሙ ወደ ዘብጥያ እንዲወርዱ ይደረጋል።

በዚህ መልኩ ያዝ ለቀቅ እያለ ከግጭት የማትረፍና በግጭት ውስጥ እየኖሩ ዓላማን የማሳለጥ መንገድ በሂደት ለዘብ ማለት እንደጀመረ የሕዝቡን አንድነት ወደ ቀደመው አብሮነቱ መራመድ ጀመረ። ይሄ ጅምር ወደ መናበብ ሲሸጋገር የእኔ የሚሉትን አማራጭ ማማተር ጀመሩ። ይህ ወቅት ምርጫ 1997 ዓ.ም የሚከወንበት ነበርና ሕዝቡ የሴራና ግጭት ጉዞው እንዲያበቃ የመናፈቁን ውሳኔ ያሳየበትን ምርጫ ከወነ። ይህ ግን በሕወሓት ቡድን ውስጥ ያልተጠበቀ ነበርና ድንጋጤን ፈጠረ፤ ድንጋጤውም የቡድኑን ግጭት የኑረቱ መሰረት አንኳር አውድ መሆኑን ተገንዝቦ በዚሁ ላይ የበለጠ እንዲሰራ አደረገው። እናም ከምርጫ 97 ማግስት ግጭቶች በረከቱ፤ ሞት፣ መፈናቀል፣ አካል መጉደል፣ አፈና፣ እስርና እንግልት መዋቅራዊ አውድ የተፈጠረላቸው እስኪመስል እንደ ሰደድ ተቀጣጠሉ።

በዚህ መልኩ ግጭት፣ ሞት፣ አካል ጉዳት፣ መፈናቀል፣ የከፋ ሰብዓዊ እንግልት፣ እስርና ቶርቸር፣... ልኩን አልፎ የሕዝብን ትዕግስት እስኪፈታተት ለአስር ዓመት ዘለቀ። ሆኖም ሞት ሞትን እንዲጋፈጥ፤ መገፋት መግፋትን እንዲለማመድ፤ መሰቃየት ስቃይንና አሰቃይን አሸቀንትሮ እንዲጥል የግድ ያለውን ሕዝባዊ እንቢተኝነት በመላው ኢትዮጵያ እንዲገለጥ፤ እንቢተኝነቱም ለውጥ እንዲወለድ አደረገ። ይህ ለውጥ ደግሞ የቡድኑን በግጭት ውስጥ ተደላድሎ የመኖር የጥፋት ጉዞውን የሚገታ ነበር።

ሆኖም የሕወሓት የጥፋት ኃይል በለውጡ ማግስት በተላላኪዎቹም በራሱም አቅም ታግዞ ንፁሃን ዜጎች በግፍ እንዲገደሉ በማድረግ በጅምላ በመቅበር አገራዊ ስጋት ለመፍጠር ሰፊ ጥረት ያደረገበት ወቅት ሆነ። ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 6ኛ ዓመት የስራ ዘመን 2ኛ ልዩ ስብሰባ ተገኝተው ከምክር ቤቱ አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት ያረጋገጡትም ይሄንኑ እውነት ነበር።

ለምሳሌ፣ ዓርማ የሌለውን ሰንደቅ ዓላማም እንዲሁ ንጹሃን ዜጎችን ለማጥፋትና ለማሳቀቅ ሲጠቀምበት የነበረው የሕወሓት የጥፋት ቡድን፤ ከለውጡ በፊት የነበረውን የሕዝብ ማዕበል ለማፈን ሲያደርገው በነበረው ሴራ የአነግን ዓርማ በገፍ በማሳተምና ዓርማውን የያዙ ሰዎችን የኢሬቻና መሰል በዓላት በሚከበሩበት ስፍራ በማስገባት ጭምር ንጹኃን ዜጎችን ለማፈን ተጠቅሞበታል። በለውጡ ሂደትም በመሪዎች ላይ ክትትል ማድረግ፣ ዛቻና ማስፈራሪያ እንዲሁም እስከ የእስር ማዘዣ ማውጣት የደረሰ አስጨናቂ የደህንነት ክትትል ሲያደርግ ነበር።

ይሄንኑ ሴራውን ከለውጡ በኋላም በማስቀጠል ቂም፣ በቀልና ጥላቻን በመተው በይቅርታ የመሻገርን ጉዞ፤ አቃፊ አገረ መንግስት የመገንባትን ትልም፤ የተሻለ ሃሳብ ይዞ ለአሸናፊነት የመብቃትን ፍላጎት በመግፋት የኖረውን የአውዳሚ ግጭት ጉዞውን የሙጥኝ ማለትን መረጠ። በዚህም በወቅቱ በጠቅላይ ሚንስትሩ ማብራሪያ ላይ እንደተመላከተው፤ ቡድኑ ሕልውናው በግጭቶች ውስጥ የተመሰረተና አትራፊነቱም በዚሁ ላይ እንደመሆኑ ከመጋቢት 2010 እስከ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም እስከፈጸመው የአገር ክህደት ተግባሩ ድረስ 113 ግጭቶችን በመላ ኢትዮጵያ ላይ አስነስቷል።

የአማራ ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት ሐምሌ 10 ቀን 2013 ዓ.ም ባወጣው መግለጫ እንዳመላከተው ደግሞ፤ የሕወሓት የጠፋት ኃይል ለዘመናት ሲሰራው የነበረውን ጸረ-ህዝብና ጸረ-ዴሞክራሲያዊ ተግባሮቹ በኢትዮጵያ ህዝቦች ፊት በተጋለጡበት ለውጥ ማግስት ከአፈርኩ አይመልሰኝ በሚል ድርጊቱ ከመጋቢት 2010 እስከ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ምየሀገር ክህደት ተግባሩ ድረስ 113 ግጭቶችን በመላ ኢትዮጵያ ላይ አስነስቷል። በእነዚህ ግጭቶች ብሔርን ከብሔር፣ ኃይማኖትን ከኃይማኖት፣ መንግሥትን ከሕዝብ፣...ወዘተ ለማቃቃር በፕሮፖጋንዳ፣ በፋይናንስ፣ በሎጀስቲክስና በሥልጠና የተደገፉ አውዳሚ ግጭቶችን ፈጥሯል። በግብሩ ልክ የቀረጻቸውን ‹ሳተላይት አሸባሪዎች› በአራቱም ማዕዘናት ለጥፋት ተልዕኮው አሰማርቶ መላ የኢትዮጵያ ብሔር ብሄረሰቦችን ወግቷል። ረፍት ነስቷል። በትህነግ እኩይ ሴራ ደም ያልፈሰሰበት የኢትዮጵያ ግዛት አካል የለም።

በዚህ መልኩ የግጭት ማዕከል ካደረጋቸው አውዶች አንዱ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተጠቃሽ ናቸው። ለምሳሌ፣ በ2012 የትምህርት ዓመት በኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የተከሰቱ ግጭቶችን እና ያደረሱትን ጉዳት አስመልክቶ የሙብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ካርድ) የተባለ ተቋም ባወጣው ሪፖርት መሰረት፤ በየዩኒቨርሲቲዎች በተነሱ ግጭቶች 12 ተማሪዎች ሕይወታቸውን አጥተዋል፤ ከ58 ተማሪዎች በላይ ቀላልና ከባድ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። ከዚህ በተጓዳኝ በ28 ዩኒቨርሲቲዎች ቀላል እና ከባድ ግጭቶች በመስተዋላቸው የመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ መስተጓጎል ፈጥሮ ነበር።

ለምሳሌ፣ ጥቅምት 30 ቀን 2012 በወልዲያ በተከሰተ ግጭት የሁለት ተማሪዎች ሕይወት ማለፉን ተከትሎ በሕዳር ወር 16 በሚሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች ግጭቶች ተስተውለዋል። ግጭቶቹም የብሔር መልክ ያላቸው ሲሆን፣ ማኅበራዊ ሚዲያዎች በሐሰተኛ መረጃዎች ግጭቶቹን የማቀጣጠል ሚና እንደተጫወቱም ተመላክቷል።

ይሄን መሰል የብሔር ግጭቶችን እዚህም እዚያም በመቀስቀስና ከግጭቶቹ ትርፉን በማስላት ሌላ የግጭት አውድ እየፈጠረ መኖር ልዩ ባህሪው የሆነው የሕወሓት የጥፋት ቡድን፤ ከትግራይ ክልል ውጪ ባሉት በሁሉም የኢትዮጵያ አከባቢዎች ላይ ግጭቶች እንዲቀሰቀሱ አድርጓል። በዚህም ንጹሃን ለሞት፣ ለአካል ጉዳት፣ ለመፈናቀል እንዲሁም ሃብት ንብረታቸውን ለማጣት ተዳርገዋል። ይሄንንም፤ "113 ግጭቶች ሲፈጠር በሁሉም ክልሎች ግጭት አለ፤ በሁሉም ክልሎች መጋደል አለ፤ በትግራይ ክልል ግን የለም። እነርሱም አያፍሩም እኛ ብቻ ነን ሰላም ይላሉ ። እዚህ ያለውን የሚያደፈርሱት እነርሱ ስለሆኑ ሁሌ የኛን ቁስል ፤ የሌሎችን ቁስል እየቆሰቆሱ በከፍተኛ ደረጃ ህዝቡን አባሉት፤" ሲሉ ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አሕመድ ሳይቀር የተናገሩትም ለዚሁ ነው።

ይሄን የሕወሓት የግጭት ነጋዴነት ተግባር በተመለከተ መረጃዎች እንደሚያሳዩት፤ ከለውጡ ማግስት በሁለት ዓመት ተኩል ውስጥ ብቻ ከተከሰቱ 113 ደም አፋሳሽ ግጭቶች መካከል፤ በኦሮሚያ 37 ደም ያፋሰሱ፣ ያፈናቀሉ እና ንብረት ያወደሙ ግጭቶች ነበሩ። በተመሳሳይ በአማራ 23 ደም ያፋሰሱ ግጭቶች የደረሱ ሲሆን፤ በቤኒሻን ጉልጉሙዝ ክልልም በተለይ የሚጠቀሱትን የመተከልና ዳንጉር ግጭቶችን ጨምሮ 15 ግጭቶች ተከስተዋል።፡

በጋምቤላ የስደተኞችን ካምፕ ጨምሮ 7 ግጭቶች ሲከሰቱ፤ በደቡብ ክልል በኮንሶ፣ በጌድዮ በጉራ ፈርዳ ንጹሀን እንዲገደሉ ንብረት እንዲወድም ያደረጉ ግጭቶች ተስተውለዋል። በሶማሌ ክልል ጅጅጋ፣ አበፋር፣ በድሬዳዋ፣ሲበዳማ እና በሀረሪ ክልሎችም መሰል ግጭቶች ነበሩ። አዲስ አበባም ብትሆን 14 ግጭቶች ተከስተውባታል። በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን አንድም ቀን በትግራይ ክልል ግጭት ተከስቶ አለማወቁ ነው የተመላከተው። ይህም በእርግጥም የሕወሓት የጥፋት ቡድን የራሱን ሕልውና ባስጠበቀ መልኩ የሚፈጽማቸው ግጭቶች በሌሎች ሞትና ስቃይ የማትረፍ ግልጽ ተግባራቱ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ነው።

በዚህ ሁሉ ግጭትና ጥፋት ውስጥ የሚፈልገውን ትርፍ ማግኘት ያልቻለው የሕወሓት የጥፋት ቡድን የመጨረሻ አማራጭ አድርጎ የያዘውን ሀገር የማፍረስ ተልዕኮ ያሳካልኛል ወዳለው ርምጃ ነው የገባው። ይሄም በተላላኪዎቹ በኩል አልሆን ያለውን በራሱ ወደመፈጸም እና ይሄንንም የአገር አጥር የሆነውን ኃይል በመናድ ማሳካት ነበር። እናም ጥቅምት 24 ቀን 2012 ዓ.ም ሌሊት የመከላከያ ሰራዊት የሰሜን እዝ አባላት ላይ በተኙበት ጥቃት ፈጸመ። በዚህም ግጭቶችን በመፍጠር ትርፍ ማግኘትን ብቻ ሳይሆን፤ ከዛ ከፍ ያለ አገር አፍርሶ የዘመናት ቅዠቱን እውን በማድረግ ውስጥ የሚገኝ ትርፍን ከፍ አድርጎ ማጣጣምን ምን ያህል ጥሙንና የባንዳነት ገጹን አደባባይ አወጣ። ተግባሩም ከግጭት ፈጣሪነት ከፍ ብሎ አገርን ወደ የጦር አውድነት የቀየረ ሆነ። መንግሥትም በመጀመሪያ ሕግ ለማስከበር ጦሩን አሰማርቶና እስከ መቐለ አዝልቆ የቡድኑን ሴል እንዲበጣጥስ ግድ አለው።

በዚህ ሂደት ግን አሸባሪው ሕወሓት የበቀል በትሩን በንጹሃን ላይ በማሳረፍ ነበር ወደዋሻው የፈረጠጠው። ለዚህ ትልቁ ማሳያ የማይካድራው በሺዎች የሚቆጠሩ ንጹሃን ላይ የፈጸመው ጭፍጨፋ ሲሆን፤ መከላከያ ሰራዊቱ እና የአማራ ክልል ልዩ ሃይል ጭምር እግር በእግር እየተከታተሉ ድባቅ ባይመቱት ኖሮ በሌሎችም አከባቢዎች ከማካድራው የባሰ ጭፍጨፋ ይፈጽም እንደነበር ጥሏቸው ያለፉቸው የግፍ ዱላዎቹ ምስክር ሆነዋል። ይህ አልበቃ ያለው የግጭት ነጋዴው ሕወሓት መከላከያ ሰራዊት ድሉን ተጎናጽፎ ለሰብዓዊነት ሲባል ከመቐሌ እንዲወጣ በተደረገ ማግስት ለሌላ ጥፋት ራሱን አደራጅቶ በመሰማራት በአማራና አፋር ክልሎች ወረራ ፈጸመ።

በዚይ ወቅትም ሌላ ከሕዝቦች ሞትና ስቃይ የማትረፍ አረመኔያዊ ተግባሩን አስመሰከረ። ከቆቦ እስከ አንፆኪያና ገምዛ፤ ከንፋስ መውጫ እስከ ባቲ፤ ከጋሊኮማ እስከ ካሳ ጊታ፤ በሁሉም በአማራና አፋር ክልሎች በወረራ በቆየባቸው ሥፍራዎች ንጹሃንን በጅምላ ጨፍጭፏል፤ ሴቶችን በቡድን ደፍሯል፤ በወንዶች ላይም ግብረሶዶም ፈጽሟል፤ ብዙዎችን ለከፋ የአካል ጉዳት ዳርጓል፤ ሥነልቡናዊ ስብራትም ፈጽሟል፤ በሙቶ ቢሊዮኖች የሚቆጠር ሃብት ንብረት ዘርፎና አውድሞ ኢኮኖሚያዊ መሰረቶቻቸውን አናግቷል፤ ዛሬም ድረስ በአስር ሚሊዩን የሚቆጠሩ ዜጎችን ለከፋ የሰብዓዊ ቀውስ ዳርጎ የሰው እጅ ጠባቂ አድርጓል።

በ1960ዎቹ ማገባደጃ ላይ ጣታቸውን ምላጭ ላይ አሳርፈው ጫካ የገቡት እነዚህ ከግጭት አትራፊ ኃይሎች፤ ግማሽ ምዕተ ዓመት የሚሆነውን ዘመናቸውን በዚሁ ተግባራቸው ተጉዘዋል። በዚህም አያሌ ወገኖችን ለሞት፣ በርካቶችን ለዘላቂ አካላዊና ስነልቡናዊ ጉዳት፣ በርካታ የሃገር ሃብት ለውድመት ሲዳርጉ፤ በአንጻሩ እነሱ ከግጭቶቹ ጀርባ ፖለቲካዊም ኢኮኖሚያዊም ግላዊ ጥቅማቸውን ሲያሳድዱ ኖረዋል። ይህ ግማሽ ምዕተዓመት የዘለቀው ግጭት እየጫሩ ከሚነደው እሳት የመሞቅ አካሄድ፤ ዛሬም በእድሜያቸው መጨረሻ ላይም ፀሐይ እየጠለቀችባቸው መሆኑን ሲያውቁ እንኳን ሊታገስላቸውና ፊታቸውን ለጸጸትና ንስሃ ሊመልሰው አልቻለም። ይልቁንም የመጨረሻ አማራጮቻቸውን አንጠፍጥፈው በመጠቀም የብሔር እንቢ ሲላቸው የሃይማኖት ግጭቶችን ደግማው ደጋግመው እየሞከሩ ሲከሽፍባቸው ማየታችን የተለመደ ሆኗል።

ከሰሞኑ ፍትህ ሚኒስቴር በጥናት ተረጋገጠ ባለው መረጃ እንዳሳወቀውም፤ አሁንም ድረስ በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች ተከስተው ከነበሩ ግጭቶች ጀርባ የአሸባሪው ሕወሓት እጅ እንዳለበት አረጋግጧል። በመረጃው እንደተመላከተውም፤ በኢትዮጵያ የመጣውን ለውጥ ተከትሎ በተለያዩ የሀገሪቷ አካባቢዎች የግጭትና አለመረጋጋት ክስተቶች ተስተውለዋል። በተለያዩ ምክንያቶች በተከሰቱት ግጭቶች የበርካታ ወገኖች ህይወት ሲያልፍ የአካል ጉዳት፣ የንብረት ውድመትና መፈናቀል ተከስቷል። በእነዚህ ወንጀሎች ላይ ከፊት ሆነው ተሳታፊ የነበሩ አካላት በሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑና ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎች ፍትሕ እንዲያገኙም ተደርጓል። ሆኖም በተለያዩ አካባቢዎች የነበሩ ግጭቶችን መንስኤ ለማጣራትና ወንጀለኞችን ተጠያቂ ለማድረግ በተደረገው ምርመራ የአሸባሪው ህወሓት የጥፋት እጆች መኖራቸው፤ የሽብር ቡድኑም ግጭቶቹን በጦር መሳሪያና በበጀት በመደገፍ እና ስምሪት በመስጠት ስለመሳተፉ ተረጋግጧል።

ይህ የሚያሳየው ደግሞ አሸባሪው ሕወሓት ትናንት በጫካ፤ በኋላም በመንግስትነት ሥልጣኑ፣ ዛሬም በሽብር ተግባሩ ሀገር እንዳትረጋጋ፣ ሕዝብም በግጭት ውስጥ ሆኖ እረፍት እንዳያገኝ በማድረግ ከግጭቱ ጀርባ የራሱን ሕልውና ማቆየት ላይ ተጠምዶ የኖረና ያለ መሆኑን ነው። ይሁን እንጂ ይሄን አይነት ሕልውናን በግጭት ውስጥ የማቆየት እና በአገር፣ በሕዝብ ብሎም በአገር ሃብት ጭዳነት የመቆመር ጉዞ ሊበቃው፤ ለዚህም መላው ኢትዮጵያውያን እውነቱን ተገንዝበው ሊታገሉት፤ የትግራይ ሕዝብም ይሄን የሞት ጠማቂ ኃይል ነጥሎ ሊያወጣው ይገባል። ይህ ሲሆን ሀገር ትረጋጋለች፤ ሕዝቦች ሰላም አግኝተው በፍቅርና በወንድማማችነት አብረው መኖር ችላሉ። አበቃሁ፤ ቸር ይግጠመን፤ ሰላም!

# ሀገር በቀል ተቋማትና አርአያነታቸው

ግርማ መንግሥቴ

አምዳችን "አገርኛ" እንደ መሆኑ መጠን ትኩረታችንም አገር በቀል ጉዳዮች ላይ አድርገናል። ለዚህም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (መያዶች)ን መቃኘት የዛሬው ርእሰ ጉዳያችን ይሆናል። በተለይም፣ ችግሮቻችንን በራሳችን አቅምና ነባር እውቀት ከመፍታት አኳያ ለማብራራት ጥረት ይደረጋል።

በሀገራችን ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አሉ። በተለይም፣ መሰረታቸው አውሮፓና አሜሪካ የሆኑ መያዶች ቁጥር ቀላል አይደለም። በተለይ ወደ ደቡብ የአገራችን ክፍል ሲኬድ የሚታየው የመያዶች ቁጥር የጉድ የሚያሰኝ ነው። ይሁን እንጂ፣ የተሰራው ስራ ሲታይ ደግሞ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም፤ ወይም ካገኘነው ያጣነው ይበልጣል ያሰኛል።

እነዚህን መሰል ችግሮች ስንመለከት መሰረታቸው አገር ውስጥ የሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቢበዙ፤ መብዛት ብቻም ሳይሆን ቢጠናከሩና በየዘርፉ ቢሰማሩ በከፍተኛ ደረጃ ለችግሮቻችን መፍትሄዎችን ያመጣሉ ተብሎ ይታሰባል። ይታሰባል ብቻም ሳይሆን ይጠበቃልና አዋጭነታቸው ከዚህ በመለስ የሚባል አይደለም።

ይህን፣ የአገር በቀል ተቋማት (መያዶቻችንን) አገራዊ ፋይዳ በተመለከተ ከዚህ በፊት በዚሁ አምድ ላይ እያንዳንዳቸውን በተናጠል በመውሰድ አላማ፣ ተግባርና ኃላፊነታቸውን፤ እንዲሁም እስከ ዛሬ ያከናወኗቸውን ሰብአዊ ተግባራት ለመፈተሽ ችለናል። የተሻለ አገልግሎት ያስመዘገቡትን የበለጠ እንዲሰሩ፤ ደከም ያሉትም እንዲጠናከሩ፤ አዳዲሶችም ወደ "መድረኩ" እንዲመጡ የሚቻለውን ጥረት ሁሉ ስናደርግ ቆይተናል። ዛሬም እንደ አጠቃላይ በመውሰድ የአገር በቀል መያዶችን አደረጃጀት፣ አላማ አፈፃፀማቸውን እያነሳን የምንነጋገር ሲሆን፤ ይህም ካሉት ጋር ከመተዋወቅም ባለፈ ወደፊት ሊፈጠሩ፤ ሊመጡ የሚገባቸውንም ከወዲሁ በመቀስቀስ ስሜት ሰጪ መልእክት ለማስተላለፍ ነው።

እዚህ ላይ አንድ አብይ ጉዳይ አስታውሶ ማለፍ ተገቢ ይሆናል። ይህ ተገቢ ጉዳይ አገር በ"አገር በቀል መያድ" እና "አገር በቀል ያልሆነ መያድ" መካከል ምን ልዩነት አለ፣ ለምንስ ሁለትን ከፍሎ ማየት አስፈለገ? የሚለው ሊሆን ቢችል፤ መልሱ ብዙም አስቸጋሪ ካለመሆኑ ጋር ተያይዞ የመጀመሪያው መልስ የሚሆነው "ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ" እንዲሉ፤ ወይም፣ በተደጋጋሚ ሲነገር እንደሚሰማው፤ በአህጉሪቱ መሪዎችም ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ሲደረግ የሚታየው "ለአፍሪካ ችግር አፍሪካዊ መፍትሄ" የሚለው ሲሆን፤ ሌላውና ዋናው መልስ ግን በውጭ የእርዳታ ድርጅት ስቃይን ከማየት፣ ጓዳ ጎድጓዳውን ለእነሱ አስረክቦ እግር ከወርች ከመታሰር፣ ባልታሰበና ባልተፈለገ የእርስ በእርስ ግጭት ውስጥ ገብቶ ከመተላለቅ (በተለይ እነሱ "ሶስተኛው አለም" በሚሉት በአፍሪካ) ... ያመለጠ አገር አለመኖሩና በጠባቂነት ስነልቦና ተቀፍድዶ መያዙ ነው። አሁን፣ ወደ ተነሳንበት፣ ወደ አገር ውስጥ መያዶች እንመለስ።

በለጋ ወጣቶች ፒያሳ አካባቢ የተቋቋመውና በእውነት ለተቸገሩ ፈጥኖ ደራሽ የሆነው "ደግ ፒያሳ" ኑሮዋ በዩናይትድ ኪንግደም፣ ኤደንብራ ከተማ ያደረገችው፤

‹‹ፀሐይ ጎልጎታ የህብረተሰብ ድርጅት›› የሚል በጎ አድራጎት ተቋም ለማቋቋም ያሰበችው፣ ባለትዳርና የሁለት ልጆች እናት የሆነችው የአርባ ምንጯ ፀሐይ አካሉ፣ በተለይ ለአረጋውያን፣ እናቶች፣ ሴቶች፣ ህፃናትና ለማረሚያ ቤት ታራሚዎች እያደረገች ያለችው ድጋፍ የሚበረታታና ሌሎችም ሊከተሉት የሚገባ አርአያነት ያለው ተግባር ሲሆን፤ በየጎዳናው የወደቁ አረጋውያንና የአእምሮ ህሙማንን በማንሳትና በመንከባከብ በገንዘብ ሊተመን የማይችል ትልቅ ሰብአዊ ድጋፍ በማድረግ ላይ የሚገኙትን፤ እነ ሜቄዶንያ፣ ሙዳይ፣ ጌርጌሲኖንና ሌሎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንም ከዚሁ ጋር አያይዞ በአርአያነት መጥቀስ ይገባል።

ይህ አርአያነት ያለው የሀገር በቀል መያዶች ተግባር፣ በተለይም ኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወደ አገራችን መግባትን ተከትሎ በጉልህ ታይቷልና እንዳይዳከም፤ የበለጠ ተጠናክሮ እንዲቀጥልና ተደራሽነቱንም እንዲያሰፋ አጠቃላይ የህዝብና መንግሥት ድጋፍ ያስፈልገዋል። ያነጋገርናቸው የ"ደጉ ፒያሳ" ወጣት አመራሮችም ያሉት ይህንኑ ነው፤ "የበለጠ እንድንሰራ፤ ተጠናክረን እንድንቀጥል የመንግሥት ድጋፍ ያስፈልገናል።"

ማህበራዊ "ኃላፊነትን ከመወጣት አኳያ፣ በዚህ በጎ ተግባር ላይ ተሳትፈው የአካባቢያቸውን አቅመ ደካማና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን እየረዱ ካሉ፤ አዲስ አበባ ውስጥ ከሚገኙ፣ መሰረታቸው ኢትዮጵያዊ (አገር በቀል) የሆነ በጎ አድራጎት ድርጅቶች መካከል አንዱ ‹‹የላምበረት ልጆች ለላምበረት ነዋሪዎች›› በሚል መርህ የተመሰረተው "የላምበረትና አካባቢው ለወገን ደራሽ የበጎ አድራጎት ድርጅት" ነው።

አቶ ደጉ መኮንን ‹‹የላምበረት ልጆች ለላምበረት ነዋሪዎች›› የሚለውን መርህ የሚያራምደው የ"የላምበረትና አካባቢው ለወገን ደራሽ በጎ አድራጎት ድርጅት" ዋና ስራ አስኪያጅ ነው። አቶ ደጉ እንደገለጸው፤ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ከመመስረቱ በፊት የላምበረትና አካባቢው ወጣቶች በራሳቸው ተነሳሽነት አቅመ ደካማና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን አረጋውያን ይረዱ ነበር።

ይሁንና በመጋቢት ወር 2012 ዓ.ም የኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ-19) ወረርሽኝ ወደ ኢትዮጵያ በተከሰተ ወቅት የላምበረትና አካባቢው ለወገን ደራሽ በጎ አድራጎት ድርጅት በሚል ህጋዊ ሰውነት ይዞ በሰባ አባላት ተመስርቷል። ድርጅቱ የተቋቋመበት ዋነኛ አላማም በተለያዩ ምክንያቶች ታመው አልጋ ላይ የቀሩ፣ አቅመ ደካሞችንና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የላምበረትና አካባቢውን ሰዎች ለመርዳት ነበር።

> **በኢትዮጵያ ቂምና በቀልን አራግፎ እርቅና ሰላም የሚወርድበት ቱባ ባህላዊ እሴት አለ፤ ሀገር በቀል እውቀት አለ። ሁሉም ብሄሮች እርስ በእርሳቸውና ከሌላውም ማህበረሰብ ጋር በሚፈጥሯቸው ጊዜያዊ ግጭቶች ባህላዊ የእርቅና የሽምግልና ሥርዓቶችን እያከናወኑ አብሮነታቸውን ሲያስቀጥሉ ኖረዋል**

ድርጅቱ እንደተመሰረተም በላምበረትና አካባቢው የሚኖሩና በውጭ ኑሯቸውን ያደረጉ የላምበረት ተወላጆች ጋር በመተባበር በአካባቢው ላይ ረጅም ጊዜ የኖሩ፣ ሰው ተጠግተው የሚኖሩና አቅመ ደካማ የሆኑ ሰዎችን በገንዘብና በቁሳቁስ መርዳት ጀመረ። በተለይ ደግሞ ወቅቱ የኮሮና ወረርሽኝ የተከሰተበት ጊዜ እንደ መሆኑ ድርጅቱ አባላቱ ገንዘብ እንዲያዋጡ በማድረግና በውጭ ሀገራት ያሉትም የአካባቢው ተወላጆች ገንዘብ እንዲልኩ በማድረግ አቅመ ደካማ ለሆኑና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የአካባቢው ነዋሪዎች ድጋፍ አድርጓል ። የበጎ አድራጎት ተግባራቸው ዝርዝሩ ብዙ ነው።

የዚህ ፅሁፍ ዋና አላማ አገር በቀል መያዶችን በብዛት ማፍራት የሚቻልበትና ከውጭ እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች መላቀቅ ወይም ነፃ መውጣት የሚገባ መሆኑን ማሳሰብ እንደ መሆኑ መጠን የ"የላምበረትና አካባቢው ለወገን ደራሽ በጎ አድራጎት ድርጅት"ን ልምድ ይካፈሉታል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። ወደ ሌላው አገር በቀል ማህበረ-ባህላዊ (በተለይም ሃይማኖታዊ) ወደ ሆነውና ወደ ተቋምነት ሊቀየር ስለሚገባው አገራዊ እሴት እንሸጋገር።

በኢትዮጵያ ቂምና በቀልን አራግፎ እርቅና ሰላም የሚወርድበት ቱባ ባህላዊ እሴት አለ፤ ሀገር በቀል እውቀት አለ። ሁሉም ብሄሮች እርስ በእርሳቸውና ከሌላው ማህበረሰብ ጋር በሚፈጥሯቸው ጊዜያዊ ግጭቶች ባህላዊ የእርቅና የሽምግልና ሥርዓቶችን እያከናወኑ አብሮነታቸውን ሲያስቀጥሉ ኖረዋል። ይህንን ደግሞ የትም ቢሄዱ ያገኙታል፣ የኦሮሚያውን ገዳ፣ የሃላባ ቁሊቶውን ሴራ ... ጨምሮ ማለት ነው። ሌሎችንም እንደዛው።

ኢትዮጵያ ስለዲሞክራሲ፣ ስለመልካም አስተዳደር፣ ስለእርቅና ሰላም ከየትኛውም ሀገር ሳትበደር ጥቅም ላይ ልታውላቸው የሚገቡ ጥሩ ጥሩ ተሞክሮዎችን ማግኘት የምትችልባቸው ባህላዊ እሴቶች ያሏት የመሆኑን ያህል፤ እነዚህን ሁሉ በተደራጀ መልኩ ስትጠቀምባቸው አትታይም። ከእነዚህና ሌሎች ቱባ ባህላዊ እሴቶች መካከል ደግሞ አንዱ የጋሞ አባቶች የሽምግልና ሥርዓት /ዱቡሻ/ እንደ ሆነ ይታውቃል። ይህ በተጠናከረና በተደራጀ መልኩ ሊቀጥል ይገባዋል።

"በጋሞ ምድር ጠብና አለማግባባት፤ ቂምና ቁርሾ የሚወገዱባቸው ጠንካራ ባህላዊ እሴቶች አሉ። የጋሞ ብሄረሰቦች ችግሮችን በባህላዊ መንገድ የመፍታት የቆየ ልምዳቸውን ጥቅም ላይ እያዋሉ ማህበራዊ መስተጋብራቸውን አጠናክረው የሚኖሩ ህዝቦች ናቸው። ልጆቻቸው ከማህበረሰቡ እሴቶች እንዳያፈነግጡ በአባቶች ምክርና ተግሳጽ ተኮትኩተው ስለሚያድጉ ለባህላዊ እሴቶች ተገዢዎች ናቸው፤ ታላላቆቻቸውንና አባቶቻቸውን ያከብራሉ፤ የሽማግሌዎችን ቃል ያደምጣሉ። " የሚለውንም የተረጋገጠና በዛ በቀውጢ ወቅት (የጋሞ አባቶች እሳት ለብሶ፣ እሳት ጎርሶ ህንፃዎችን ለማጋየት የመጣውን የተቃውሞ ሀይል ቄጤማ ይዘው በመንበርከክ እንዴት እንደመለሱት) በአይናችን የተመለከትነው እውነት እዚህ ሊጠቀስ ይገባዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር አቢይ አሕመድ በወቅቱ በጋሞ የሰላምና ሽምግልና አባቶች ስም አንድ የሰላም ተቋም ይገነባል ማለታቸው የሚታወስ ሲሆን፤ ይህም፣ ከተደረገ ማለት ነው፣ እዚህ በተደራጀና በተጠናከረ መልኩ ... እያልን ያለነውን ሃሳብ የሚያጠናክር ነው።

በቅርቡ በሀገራችን ተከስቶ የነበረውን አስቸጋሪና መደገም የሌለበትን አፍራሽና በርካታ ቤተ-እምነቶችን ዶጋ አመድ ያደረገ፤ የበርካታ ንፁሀንን ሕይወት የቀጠፈ ተግባር አስመልክተው፤ "ለመሆኑ ሃይማኖተኛ ሆኖ በሌላ ሃይማኖት ላይ ያነጣጠሩ ጥቃቶችን መፈጸም ምን ያህል ከሃይማኖቶች አስተምህሮ ጋር አብሮ ይሄዳል?" በሚል ማእከላዊ ጥያቄ (ጭብጥ) ዙሪያ ሃሳባቸውን ያካፈሉ የሁለት ሃይማኖቶች (ክርስትና (ኦርቶዶክስ ተዋህዶ) እና እስልምና) አባቶች (መጋቤ ካህናት አባ ሀብተጊዮርጊስ አሥራት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የገዳማት መምሪያ ዋና ኃላፊ፤ እንዲሁም፣ ነዋሪነታቸው አዲስ አበባ፣ አራዳ ክፍለ ከታማ፣ ወረዳ ሁለት የሆነው ሼህ ሙሐመድ አሊ ሙሳ እንዳሉት፤ ድርጊቱ በማንኛውም መስፈርት የሚደገፍ አይደለም።

እዚህ ላይ ድርጊቱ በሃይማኖት በኩል የማይደገፍ መሆኑን ከመግለፃቸው ባለፈ ሁለቱም አባቶች (ሁለቱም ባልተገናኙበትና ምንም በማይተዋወቁበት ሁኔታ) የሰጡት ማብራሪያ በአንድ ምሳሌ (ልዩነታቸውንና አንድነታቸውን የገለጹበት መንገድ) የተደገፈ መሆኑ ሲሆን፤ ይህም ሙስሊምና ክርስቲያን በዋና ሃይማታዊ ጉዳዮቻቸው ቢለያዩም በብዙ ነገሮች ይመሳሰላሉ። በአንድ ወቅት ሁለቱም የየራሳቸውን ከብት ባርከው ካረዱ በኋላ በተለያየ ክር እያሠሩ በአንድ እቃ ይቀቅሉታል። ከዚያም ሲበስል አውጥተው የየራሳቸውን ይመገባሉ። እንግዲህ ስጋው አንድ ላይ ሲቀቀል በመረቁ መነካካቱ አይቀርም፤ የሁለቱም ሃይማኖት ተከታዮች በማህበራዊ ህይወታቸው ብዙ የሚጋሯቸው፤ የጋራ የሆኑ እሴቶች አሏቸው። በበርካታ ጉዳዮች የተሳሰሩ ስለ መሆናቸው ጥሩና ወቅታዊ ማሳያ ሲሆን፤ ልዩነትንም አንድነትንም አክብሮ አብሮ መኖር እንደሚቻል በምሳሌ ያረጋገጡበት ቃለ መጠይቅ ነበር።

ከዚህ ምሳሌ በተጨማሪ፣ አሁን ያለውም ሆነ ወደ ፊት የሚመጣው ትውልድ የቀደሙት አባቶቹ እንዴት ተስማምተውና ተከባብረው እንደኖሩና እንደሚኖሩ በሚገባ መረዳት እና እሱም ያንኑ የበለጠ አጠናክሮ ማስቀጠል ያለበት መሆኑንም ነው የሃይማኖት አባቶቹ በመልእክታቸው የተናገሩት። "የሃይማኖት አባቶች ወጣቶችን እየሰበሰቡ ማስተማርና መምከር እንደ ቀዳሚው ዘመን ተከባብረንና ተመካክረን እንድናድር ማድረግ አለባቸው። መንግሥትና የሚመለከታቸው አካላት (ተቋማት) ችግር ከመድረሱ በፊት ፈጥኖ በመድረስ አጥፊዎችን እየተከታተሉ እርምጃ መውሰድ (ለህግ ማቅረብ) ይኖርባቸዋል። " የሚለውም መልእክታቸው ነበር።

በአጠቃላይ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ማለት ይቻላል። ዋናውና መሰረታዊው ጉዳይ ግን እጅ እየዘረጉ፣ አላማቸው ምን እንደሆነ እንኳን በውል ሳይታወቅ፣ የውጭ እርዳታ ድርጅቶችን መቀበል መብቃት አለበት። እንደነ ቻይና ራሳችንን ችለን ለሌሎችም የምንተርፍበት መንገድ ከወዲሁ ሊመቻች ይገባል። የበርካታ አገር በቀል እውቀቶች፣ እሴቶች፣ ትውፊቶች ... (ለዛውም "የሚዳሰሱ" እና "የማይዳሰሱ" የሚሉትን ሳናካትት) ባለቤቶች ነንና እነሱን ወደ ተቋማት በመቀየር ከራሳችን ሀብት ራሳችን ተጠቃሚ እንሁን፤ ለዚህ ደግሞ የጋራ ግንዛቤ፣ የጋራ ራእይ፣ የጋራ ግብ ... ያስፈልጋል የሚለው ነውና በዚሁ እንሰናበታለን።

# የሥራ ፈጠራ ፅንሰ ሀሳብ ስልጠና - ለወጣቶች

**አስናቀ ፀጋዬ**

ኢትዮጵያ በርካታ ቁጥር ያለው የተማረና ያልተማረ ወጣት የሚገኝባት ሀገር ናት። ይህ የሕዝብ ቁጥር መብዛት ታዲያ አንድም እንደ መልካም እድል የሚቆጠር ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ስጋት ይታያል ። በርካታ ቁጥር ያለው ትኩስ ኃይል ወደ ሥራ ቢሠማራ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በእጅጉ የሚያሳድግ በመሆኑ እንደመልካም አጋጣሚ ሊቆጠር ይችላል። ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ ለዚህ የወጣት ኃይል በበቂ ሁኔታ የሥራ እድል መፍጠር ካልተቻለ በቁጥሩ ልክ ስጋቶች መፈብረካቸው አይቀሬ ነው።

ሀገሪቱ ካላት በርካታ ቁጥር ያለው ወጣት አኳያም ሰፊ የሥራ ዕድል የሚፈጥር በርካታ ሥራ እየተሠራ ነው። ሰፊ የሰው ኃይል ለሥራ የሚያሠማሩ ባለሀብቶች ወደ ሀገሪቱ እንዲገቡ ፣ ኢንዱስትሪዎች በመላው ሀገሪቱ እንዲስፋፉ መንግሥት ሳያሰልስ እየሠራ ይገኛል። ወጣቱ የተለያየ ስልጠና እንዲያገኝ በማድረግ ረገድም የሚሠሩ ሥራዎች ብዙ ናቸው። በእርግጥ ይህም ቢሆን በመንግሥት ብቻ የሚከናወን አይደለም። የግል ባለሀብቱ የራሱ የወጣቱም ድርሻ ጉልህ ነው። በራሳቸው ሰልጥነውና ሥራ ፈጥረው ለብዙ ወጣቶች የሥራ ዕድል የከፈቱና ለብዙዎች ሞዴል የሆኑ ወጣቶችም አሉ። ሆኖም ግን ወጣቱ የሥራ እድል መፍጠር ከዚያም ወጥቶ መሥራትን ይጠይቃል። በተለይ ወጣቱ በራሱ ሥራን እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ማመቻቸት ከምንም በላይ ለችግሩ እልባት ይሰጣል። ይህንን ማድረጉ ደግሞ ከመንግሥትና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ይጠበቃል። ወጣቱም ቢሆን በራሱ የሚያደርገው ትግል ወሳኝ ነው።

ስለሥራ ፈጠራ ፅንሰ ሃሳብ ሲነሳ በብዙዎች ዘንድ ወደ አዕምሮ የሚመጣው በመንግሥት በኩል ለወጣቶች የሚመቻቸው የሥራ እድልና ወጣቶች በራሳቸው ሥራ ፈጥረው ተጠቃሚ የሚሆኑበት የቢዝነስ አካሄድ ነው። ይሁንና ሥራ ፈጠራ የግድ መንግሥት ባመቻቸው የሥራ እድል ተጠቃሚ መሆን ብቻ አይደለም። የራስን ቢዝነስ መጀመር ብቻም ሊሆን አይችልም። ከዚያም የላቀ ነው። በግልም ሆነ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ተቀጥሮ በመሥራት አዳዲስ ሃሳቦችንና አሠራሮችን በመፍጠር ውጤታማ ሥራዎችን ማከናወንም ጭምር እንደሚያካትት ባለሙያዎች ይናገራሉ።

በተለይ በአሁኑ ጊዜ በመንግሥት ተቋማት ውስጥ አዳዲስ የዩኒቨርስቲ ምሩቃን ወጣቶች በብዛት እየተቀጠሩ ያሉ በመሆናቸው ተቋማቸውን ፈጠራ በታከለበትና በሁለንተናዊ መልኩ ሊለውጡ ይገባል። ስለ ሥራ ፈጠራ ፅንሰ ሀሳብ ጠንቅቀው የሚያውቁትም ይህንን ተግባራዊ ሲያደርጉ ነው። ይህንን ተመርኩዞ በቅርቡ የኢንተርፕሪነርሺፕ ኢንስቲትዩት በራሱ ተነሳሽነት በትላልቅ የመንግሥት ተቋማት ውስጥ ለሚሠሩ ወጣቶችና ለሌሎች አንጋፋ ሠራተኞች በሥራ ፈጠራ ፅንሰ-ሃሳብ ዙሪያ ስልጠናዎችን ሰጥቷል።

ስልጠናዎቹ በተለይ ወጣት የመንግሥት ተቋማት ሠራተኞች የእውቀት አድማሳቸውን በማስፋት በተቋማቸው ፈጠራ የታከለባቸውን ሥራዎች እንዲያከናውኑና ተቋማቸውን እንዲለውጡ የሚያግዝ ስለመሆኑ ተነግሯል።

አቶ ቦሩ ሻና በኢንተርፕሪነርሺፕ ልማት ኢንስቲትዩት የሰለጠነና ፕሮግራም ማናጀር ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፤ በሥራ ፈጠራ ፅንሰ ሃሳብ ዙሪያ በከፍተኛ የመንግሥት ተቋማት ለሚሠሩ ወጣቶችና ልምድ ላላቸው ሠራተኞች ስልጠና መስጠት የተፈለገበት ዋነኛ ዓላማ አስተሳሰቡ በውስጣቸው ሰርፆ እንዲገባና መንግሥት በኃላፊነት ደረጃ ያሉ ሠራተኞቹ በየመሥሪያ ቤቱ የተቀላጠፈና ኃላፊነትን የወሰደ ሥራ እንዲያከናውኑ በመፈለጉ ነው።

ስልጠናው ከተለመደው አሠራር ወጥተው አዳዲስ አሠራሮችን በሚሠሩበት መሥሪያ ቤት እንዲያመጡና ከችግሮች ፊት እየቀደሙ የማኅበረሰቡን ችግር እየፈቱ እንዲሄዱ የሚያስችልም ጭምር ነው። ከዚህ በፊት ሥራ ፈጠራ በብዛት የሚታወቀው በግል ሴክተር ቢሆንም የአሁኑ ግን አዲስ አሠራር ነው።



አቶ ቦሩ ሻና

ፎቶ- በአስናቀ ፀጋዬ

ኢንተርፕሪነሺፕ ሲባል ደግሞ ለግል ሴክተር ብቻ የተሰጠ አጀንዳና ቢዝነስ መሥራት ብቻ አይደለም። ከዚህ ይልቅ ኢንተርፕሪነርሺፕ ሁሉም ሰው በተሠማራበት የሥራ መስክ አዳዲስ እሴቶችን ጨምሮ ለሚያገለግለው ኅብረተሰብ በየጊዜው የተሻሻለ አሠራርና ሥራን የሚያመጣበት ነው።

የኢንተርፕሪንሺፕ ፅንሰ ሃሳብ ሰዎች ሥራን በፍቅር እየሠሩና ችግሮችን እየፈቱ ፈጠራን ያማከለ አሠራር እንዲኖር የማድረግ አስተሳሰብ ጭምር ነው። ሰውን በፍቅር የማገልገል፣ ችግሮ ሲፈጠሩ በፍጥነት እየቀረፉ የመሄድና ኃላፊነት እንዲሰማ የሚያደርግም ነው። ከዚህ አንፃር እሴት መጨመር በገንዘብ ብቻ የሚለካ ሳይሆን በተቋሙ ውስጥ ያሉ ሠራተኞችም ፈጠራን ያማከለ አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻል ነው።

በዚህ ፅንሰ ሀሳብ ደምበኛም የሚማረርበት ሳይሆን በየጊዜው አዳዲስና የተቀላጠፈ አገልግሎት አግኝቶ የሚረካበት ነው። ከላይኛው አመራር እስከታችኛው እርከን ያሉ የመንግሥት ሠራተኞችም በዚሁ አስተሳሰብ እንዲቃኙ የሚያስችል ነው።

አቶ ቦሩ እንደሚሉት፤ በሥራ ፈጠራ ፅንሰ ሀሳብ ዙሪያ እንዲህ አይነቱ ስልጠና ለወጣቶችና ልምድ ላላቸው ሠራተኞች ሲሰጥ የመጀመሪያው ነው። በሀገር ደረጃ እንደስትራቴጂ ተቀምጦ ያለው የግል ሴክተሩ ኢኮኖሚውን እንደሚያነቃቃ ነው። ይሁን እንጂ ይህ አዲስ የሥራ ፈጠራ አስተሳሰብ የመንግሥት ሴክተር እንዲሻሻልና ፈጣሪ እንዲሆን በሴክተሩ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል። በዚሁ ፅንሰሃሳብ መነሻ መንግሥትም በራሱ ኃላፊነት ወስዶ ለግል ኢንተርፕሪነርሺፕ ዘርፍ ምቹ ሁኔታዎችን እንዲያመቻች ተደርጓል።

የግሉ ሴክተር ለብቻው ውጤታማና ሥራ ፈጣሪ ሊሆን አይችልም። በተመሳሳይ የመንግሥት ሴክተርም የተንዛዛና ብቁ ያልሆነ አገልግሎት መስጠት የለበትምና ይህ የሥራ ፈጣራ ፅንሰሃሳብ በሁለቱም ሴክተሮች ውስጥ መስረፅ ይገባዋል። በተለይ ደግሞ የመንግሥት ሴክተር የሥራ ፈጠራ ፅንሰሃሳብ በገባቸው ሰዎች ሊመራ ይገባል። ከዚህ አንፃር በተለይ ትኩስ ኃይል የሆኑት ወጣቶች ይህ እድል በእጅጉ ያስፈልጋቸዋል።

በአሁኑ ወቅት እየመጣ ያለው ወጣትም ሆነ ጊዜ እየተቀየረ ነው። በተመሳሳይ የዓለም አቀፍ ሁኔታም ተለዋዋጭ ነው። በዚያው ልክ ሀገሪቱ ከሌሎች ሀገራት ጋር በተለያየ መስክ የምታደርገው ወድድርም ጨምሯል። የዛኑ ያህል ዘርፈ ብዙ ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮችም እያጋጠሙ ይገኛሉ። እነዚህ ሁኔታዎች ተቋቁሞ ለመሄድ ደግሞ አሁናዊ ሁኔታዎችን ተረድቶ መሥራት የሚችል የሰው ኃይል መገንባት ያስፈልጋል።

የመንግሥት ሴክተር ውስጥም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውና እምቅ ችሎታን ያነገቡ ነገር ግን በአግባቡ ያልተጠቀሙበት ወጣቶች አሉ። በተመሳሳይ በሚሠሩት ሥራ ምቹ ሁኔታዎች ሲፈጠርላቸው አዳዲስ አስተሳሰቦችን የሚፈጥሩ ይኖራሉ። ወጣቶች ይበልጥ ለቴክኖሎጂ ቅርብ በመሆናቸውና አዳዲስ ነገሮችን የመቀበል ችሎታቸው የላቀ በመሆኑ ይህንን እያዩ መጠቀሙ ከምንም በላይ አስፈላጊ ነው።

ዘመኑ በፍጥነት አዳዲስ ነገሮችን በቶሎ የመያዝና ወደውጤት መቀየርን ይፈልጋል። የሥራ ፈጠራ ፅንሰ ሃሳብም ይህንኑ የሚያቀነቅን ነው። እናም ከዚህ አንፃር ረጅም ዓመታትን የሠሩ ሰዎች ሳይሆኑ ገና በለጋ አዕምሯቸው የሥራውን ዓለም የተቀላቀሉ ወጣቶች አዳዲስ የሥራ ፈጠራዎችን የማምጣት ችሎታ አላቸውና ነገሩን እንዲረዱትና ወደተግባር እንዲገቡበት ማድረግ ከምንም በላይ ያስፈልጋል።

እንደ አቶ ቦሩ ገለፃ፤ የዚህ ሥራ ፈጠራ ፅንሰሃሳብ ስልጠና መጀመር በተለይ በፐብሊክ ሰርቪስ ውስጥ ያሉ ወጣቶች በውስጣቸው ያለውን እምቅ ችሎታ በማውጣት እንዲጠቀሙ ያስችላቸዋል። ተቀጥረው ሲሠሩ ራሳቸውን በማየት የራሳቸውን ቢዝነስ ለመጀመርም በር ይከፍትላቸዋል። በተጨማሪም የፐብሊክ ሴክተር በጣም የታጨቀና አብዛኛው ሠራተኛም ከአቅም በታች እየሠራ ያለ በመሆኑ በዚህ የሥራ ፈጠራ ፅንሰሃሳብ አስተሳሰብ ወጣቶች አቅማቸውን አውጥተው እንዲጠቀሙ ያስችላቸዋል።

ደምበኛውም የተቀላጠፈና እርካታ ያለው አገልግሎት እንዲያገኝ ያደርጋል። ከዚህ ባለፈ ወጣቶቹ የራሳቸውን ቢዝነስ ለመጀመርም እንደመንደርደሪያ ስለሚሆን ስልጠናው እንደመልካም አጋጣሚ ይቆጠራል።

የስልጠናው ፕሮግራም የሥራ ፈጠራ አስተሳሰብን በፐብሊክ ሰርቪስ ሴክተሩ አገልጋዮች ውስጥ የማስረፅ ዓላማን ብቻ የያዘ አይደለም። ይልቁንም ሠራተኛው ሥራ ፈጣሪ እንዲሆን፣ ጠንካራ የሥራ ባህልን እንዲያዳብርና በዚሁ ደረጃ ሀገሪቱን እንዲመራት ማድረግም ጭምር ነው።

ጽንሰ ሀሳቡ በግሉ ሴክተር ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶች ያሉ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ የወጣቶች የሥራ ፈጠራ ፕሮግራም አንዱ ነው። በተለይ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚመረቁና እየተመረቁ ያሉ ወጣቶች የሥራ ፈጠራ አስተሳሰብ እንዲኖራቸውና በዚሁ ልክ እንዲሠሩ ከዩኒቨርስቲዎች ጋር የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም እየተሠራ ይገኛል።

ወጣቶች በውስጣቸው ያለውን እምቅ ችሎታ ማውጣት እንዲችሉ የኢንተርፕሪነርሺፕ ስልጠና ፕሮግራሞች ይዘጋጃሉ። በሥራ ፈጠራ ዙሪያ በወጣቶች መካከል ውድድሮችም ይካሄዳሉ። በዚህ ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎችም በኢንስቲትዩቱ በኩል ይሰጣሉ። ወጣቱን ጨምሮ የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኛው የሥራ ፈጠራ ፅንሰ ሃሳብን እንዲጎለብት በኢንስቲትዩቱ በኩል የተጀመረው ተግባር በሀገር አቀፍ ደረጃ የሥራ ፈጠራ ውጤት እንዲጨምር ያደርጋል።

ሰዎች በሚሠሩባቸው የግልም ሆነ የመንግሥት ተቋማት ውስጥ ኃላፊነት ወስደው ሌላ አካል ከውጪ ይጠይቀኛል ብለው ሳይጠብቁ ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ያስችላቸዋል። ይህ ደግሞ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚጨምረው እሴት ይኖራል። እንዲህ ዓይነት ሰዎች በብዙ ቁጥር ደግሞ ፐብሊክ ሰርቪስ ውስጥ ያለው ሥራና አሠራሮቹ በየዓመቱ እየተሻሻለና እየተቀላጠፈ ይሄዳል። ይህም የተደሰተና የለማ ማኅበረሰብ እንዲፈጠር ያደርጋል።

ተገልጋዮች ችግራቸውን አይቶ መፍትሔ ሰጪ ትውልድ እንዲያገኙ ያግዛል። በተመሳሳይ በመንግሥት ሴክተር ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች በተለይ ለግሉ ዘርፍ ሥራ ፈጣሪዎች ምቹ ሁኔታ እንዲፈጥሩ ያደርጋል። ለዚህ ደግሞ ትልቁን ኃላፊነት መንግሥት ይወስዳል። የድህነትና የሥራ አጥነት ችግርን በመቅረፍ ረገድም ሚናው የጎላ ነው።

አሁን ላይ የሚታየውን የውጪ ምንዛሪ እጥረትን መቅረፍ የሚቻለውም የሥራ ፈጠራ እንቅስቃሴዎች በብዛት ሀገሪቱ ላይ ሲኖሩ ነው። የሥራ ፈጣሪዎች ቁጥር ሲበዛ ደግሞ ምርታማነት ይጨምራል፤ የሀገሪቱ ዓመታዊ የተጣራ ምርት በየዘርፉ ይሰፋልም። ከዚህ ባለፈ ሥራ አጥነት ይቀንሳል። ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባን ምርት በሀገር ውስጥ መተካትና የሚወጣውን የውጪ ምንዛሪ ማዳን ያስችላል። እንዲሁም ወደ ተለያዩ ሀገራት የተለያዩ ምርቶቻቸውን የሚልኩ ኢንተርፕራይዞች ይበዛሉ። ይህ ደግሞ አሁን የሚታየውን የውጪ ምንዛሪ ችግርን ያሻሽለዋል። በዓለም አቀፍ ደረጃ የሀገሪቱ ተወዳዳሪነትም ከፍ እንዲል ያደርጋል።

የኢንተርፕሪነርሺፕ ልማት ኢንስቲትዩት በቅርቡ ባዘጋጀው የሁለት ዙር የሥራ ፈጠራ ስልጠና ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴርና ከመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስቴር ጋር በተደረገ የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት 60 የሚሆኑ ከፍተኛና መካከለኛ አመራሮች እንዲሁም በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኙና በተለያዩ የሥራ ዕርከኖች ላይ የሚገኙ ወጣት ሠራተኞች ተሳትፈውበታል።

# የምድር በረከት

# የማዕድን ዘርፉ ፀጋዎችና የማልማቱ ተግዳሮቶች

**ስምስም መንግሥቱ**

ኢትዮጵያ በማዕድን ሀብቷ ትታወቃለች። ለኢንዱስትሪዎች ግብዓቶች የሆኑ ማዕድናትና እሴት የተጨመረባቸው የማዕድን ውጤቶችን በስፋት ጥቅም ላይ እያዋለች የምትገኘው ግን ከውጭ በማስገባት ነው። ለእዚህም በየዓመቱ በቢሊዮን ዶላር ወጭ እንደምታደርግ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ የሚስተዋለው የምርትና አገልግሎቶች ዋጋ መናር ደግሞ የኢኮኖሚ አቅሟን እየተፈታተነው ይገኛል። በቂ የውጭ ምንዛሪ አቅም ባለመኖሩ ግብዓቶቹን በሚፈለገው መጠንም ወደ ሃገር ውስጥ ማስገባት የማይቻልበት ሁኔታም እየታየ ነው። ይህ ደግሞ በግንባታው ዘርፍ እስከ ከፍተኛ ደረጃ የሚገኙ ፕሮጀክቶች በሲሚንቶ፣በብረት፣ለግንባታ ማጠናቀቂያዎችና ሌሎችም አስፈላጊ የሆኑ የማዕድን ውጤት ግብዓቶች ዋጋ መናር ሥራዎች እንዲጓተቱ ምክንያት እየሆነ ነው።

የሃገሪቱ የኢኮኖሚ ዋልታ ለሆነው የግብርናው ዘርፍ የሚውለው የማዕድን ውጤት የሆነው ማዳበሪያም አቅርቦት ችግር ይስተዋልበታል። ለማዳበሪያ ግብዓት የሚሆን የማዕድን ሀብት ሃገር ውስጥ በበቂ መጠን እያለ ጥቅም ላይ ባለመዋሉ ግዥው ከውጭ ይፈጸማል። ዓለም ላይ ያለው የማዳበሪያ ዋጋ ደግሞ እየናረ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ሃገሪቱ በእዚህ ሁሉ ቁጭት ውስጥ ሆና እንደ ማዳበሪያ ፋብሪካ ያሉትን ለመገንባት ከፍተኛ መጠን ያለው ሀብት መድባ ጥረት ብታደርግም ሊሳካላት አልቻለም። በእዚህና በመሳሰሉት ችግሮች ሳቢያ የማዕድን ዘርፉ የሚፈለገው ደረጃ ሊደርስ አልቻለም።

ሃገሪቱ ከራስዋ አልፎ ለውጭ ገበያ በማዋል የውጭ ምንዛሪ ግኝትን በማሳደግ መጠቀም የሚያስችላት የምድር ውስጥ ፀጋ ቢኖራትም፣ ባለመልማቱ የተነሳ የውጭ ናፋቂ ሆና ቀጥላለች። የሚገርመው ደግሞ በውጭ ምንዛሪ ወደ ሃገር የምታስገባው ለግብዓትነት የሚውል የማዕድን ውጤት በከፍተኛ የጥራት ደረጃ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ሆኖ በሃገር ውስጥ ግብዓት መጠቀም ውስጥ አለመገባቱ ነው፤ ይህም የማዕድን ዘርፉን የሚመራውን አካል ጭምር ቁጭት ውስጥ ከትቶታል።

ይህን ቁጭት ወደ ተግባር ለመለወጥ ማዕድን ሚኒስቴር ማዕድናትን የማስጠናት ፣አዋጭነታቸውን የማስገመገም ጥናት እንቅስቃሴውን አጠናክሯል። ዘርፉን ወደፊት ሊያራምደው የሚችል ፖሊሲ ከመቅረጽ አንስቶ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል።

የማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ታከለ ኡማ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን የ2014 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት የእቅድ አፈጻጸም እና ወደፊት መከናወን ስላለባቸው ተግባራት ባለፈው ማክሰኞ ለሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት በዓለም ላይ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችል፣የሃገር ኢኮኖሚንም የሚያሳድግ በአብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል ምድር ውስጥ እምቅ የማዕድን ሀብት ይገኛል ሲሉ ገልጸው፣ ኢትዮጵያ በማዕድን ዘርፍ የተጓዘችበት መንገድ የእሳቤ ችግሮችና ሳንካዎች ነበሩበት ሲሉ አስታውቀዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ የተፈጥሮ ሀብትን እንደ ፀጋ ሳይሆን፣እንደ ግጭት መንስኤ አድርጎ በመውሰድ፣ የጠራ እይታ ባለመኖሩና በመሳሰሉት ምክንያቶች ሀብቱ እያለ ግን እንደሌለ ተደርጎ ሲታይ ቆይቷል። የማዕድን ዘርፉን የሚመጥን ፖሊሲ ተቀርጾ ሥራ ላይ አለመዋሉ፣ተቋማዊ አደረጃጀቱም ችግር ያለበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለአጠቃላይ ሃገራዊ ምርት ያለው አበርክቶ በዚያው ልክ ዝቅተኛ እንዲሆን እንዳደረገው ካለፉ የዕቅድ አፈጻጸሞች ሚኒስቴሩ ተገንዝቧል።

እንደ ሃገር የኢኮኖሚና የፖለቲካ መዋቅራዊ ለውጥ ከተደረገባቸው ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ ግን የማዕድን ዘርፉ ከኢኮኖሚ ምሰሶዎች አንዱ ሆኖ ትኩረት አግኝቷል ያሉት ኢንጂነር ታከለ፣ በአስር ዓመቱ የሃገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ መሪ እቅድ ላይም ከአምስቱ ምሰሶዎች መካከል አንዱ የማዕድን ዘርፉ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም ተቋሙን በአዲስ መልክ ሲያደራጅ፣የማሻሻያ ሥራዎችን ሲሠራ ሃገራዊ ዕቅዱንና የማዕድን ዘርፉ የሃገር ኢኮኖሚን መሸከም የሚችል መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት መሆኑን አመልክተው፣ በዚሁ መሠረትም ሚኒስቴሩ በ2014 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት፤ ወጪ ንግድን ማሳደግ፣የገቢ ምርቶችን በሃገር ውስጥ መተካትና ለዜጎች የሥራ ዕድልን መፍጠር በሚሉ ሥራዎችን ከፋፍሎ ማከናወኑን ያብራራሉ።


ፎቶ- አዮብ ተፈራ

የማዕድን ሚኒስትሩ ኢንጂነር ታከለ ኡማ ከምክር ቤቱ አባላት የቀረቡትን አብዛኛቹን አስተያየቶች በግብዓትነት ወስደዋል ፤ ችግሮችን ለመፍታት የምክር ቤቱን ድጋፍ ጠይቀዋል፤

ኢንጂነር ታከለ እንዳብራሩት፤ ሚኒስቴሩ በዘጠኝ ወር አፈጻጸሙ ለውጭ ገበያ ከቀረቡ የወርቅ፣ጌጣጌጥና የኢንዱስትሪ ማዕድናት 458 ነጥብ 07 ሚሊዮን ዶላር ገቢ አስገኝቷል። ለወጪ ገበያ ከሚቀርቡት ማዕድናት በተጨማሪ ለሃገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎችና ለግንባታ ዘርፍ የሚቀርቡ የተለያዩ ማዕድናት የሚገኙ ሲሆን፣አራት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ቶን የኢንዱስትሪ ማዕድናት ምርት ለኢንዱስትሪዎች ቀርቧል።

የማዕድን ዘርፉ በብዛት፣በጥራትና በዓይነት በሃገር ኢኮኖሚ ላይ አበርክቶ እንዲኖረው ሲሠራ የአካባቢው ማኅበረሰብ የዘርፉ ተጠቃሚነትም አልተዘነጋም። በዘጠኝ ወር የሥራ እንቅስቃሴ ለ126ሺ ዜጎች የሥራ ዕድል የሚፈጥር ተግባር ማከናወን ችሏል። ሚኒስቴሩ ጎን ለጎንም ከፍተኛ ልፋትና ጉልበት የሚጠይቀውን የማዕድን ዘርፍ ሥራ በቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን የፈጠራ ውጤቶች ወደ ሥራ እንዲገቡ እያደረገ ይገኛል።

ባለፉት ዓመታት በማዕድን ዘርፉ የሃገር ውስጥም ሆነ የውጭ የግል ኢንቨስትመንቶች ተሳትፎ በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ መሆኑንም አስታውቀዋል። ከተለያዩ ሃገሮች የሚቀርቡ በዘርፉ እንሰማራ ጥያቄዎች እያደጉ መምጣቸውን ገልጸው፣ ይህም ለማዕድን ዘርፉ ተስፋ ሰጪ መሆኑን ተናግረዋል።

ከኢንዱስትሪ ግብአቶች አንዱ የሆነውና ለሲሚንቶ ፋብሪካዎች የኃይል ግብዓት የሚውለውን የድንጋይ ከሰል በሃገር ውስጥ ለመተካት ጥቂት ወራት ብቻ መታገስ እንደሚገባ ያስገነዘቡት ሚኒስትሩ፣ በሚቀጥለው በጀት ዓመት የድንጋይ ከሰል ከውጭ በግዥ ማስገባት እንደሚቆም ለምክር ቤቱ አረጋግጠዋል።

በአሁኑ ጊዜ በኦሮሚያ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በደቡብና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች የድንጋይ ከሰል ለማምረት በፋብሪካ ግንባታ ላይ በሚገኙ ኩባንያዎች ላይ ተስፋ ተጥሏል ሲሉ ገልጸው፣ ኩባንያዎቹ ሥራቸው ሰምሮ እቅዱ እንዲሳካ የባለድርሻ አካላት ያላሰለሰ ትብብር እንደሚያስፈልግ ሚኒስትሩ አስታውቀዋል።

በተመሳሳይ ለብረት ማዕድንም ትኩረት መሰጠቱን ሚኒስትሩ ጠቅሰዋል። እንደ ሚኒስትሩ ማብራሪያ፤ በሃገር ውስጥ ብረት አምራች ፋብሪካዎች ቢኖሩም፣ ፋብሪካዎች በግብዓት በኩል ከውጭ ሃገር ከሚገባ ግብዓት የተላቀቁ አይደሉም። በሃገር ውስጥ የሚገኘ ጥሬ ዕቃን አይጠቀሙም። ክፍተቱን በመለየት በሃገር ውስጥ በመተካት የውጭ ምንዛሪ ወጭን ለማስቀረት ጥረት እየተደረገ ሲሆን፣ ችግሩንም በአጭር ጊዜና በረጅም ጊዜ ለመፍታት እየተሞከረ ነው።

የብረት ግብዓት አቅርቦት ችግርን ለመፍታት ሚኒስቴሩ በጊዜያዊነት የወሰደው የመፍትሔ እርምጃ በግንባታው ዘርፍ ላይም ሆነ በሥራ ላይ የሚገኙ ፋብሪካዎች በግብዓት እጥረት ሥራቸው እንዳይስተጓጎል፣ ከመከላከያ ሚኒስቴርና ከሌሎች መንግሥታዊ ተቋማት 386ሺ ቶን ስብርባሪ ብረቶች በመጠነኛ ዋጋ በግዥ እንዲያገኙ ተመቻችቷል። የውጭ ምንዛሪ የማግኘት ችግርም በመጠኑም ቢሆን እንዲፈታላቸው ተደርጓል።

ሚኒስቴሩ ዘላቂ መፍትሔ ብሎ ያስቀመጠው የሃገር ሀብትን መጠቀም መሆኑንም ኢንጂነር ታከለ ጠቁመዋል። የብረት ምርት አቅርቦትን ሙሉ ለሙሉ በሃገር ውስጥ ለመተካት ሚኒስቴሩ በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች ከፍተኛ የብረት ማዕድን ጥሬ ሀብት ክምችት መኖሩን የሚያሳይ የጥናት ሰነድ በማዘጋጀት የቅድመ አዋጭነት ግምገማ ጥናት እያከናወነ ይገኛል ብለዋል።

በጥናት የተገኙ የክምችት ናሙናዎችን በቤተሙከራ ውስጥ(ላቦራቶሪ)የማረጋገጥ ሥራ እየተከናወነ ሲሆን፣ ብረት ለማምረት የሚያስፈልጉ ጥሬ ማዕድናት ማለትም ብረት አዘል አለት፣ኖራ ድንጋይ፣የድንጋይ ከሰልና የመሳሰሉ መጠናቸውና የጥራት ደረጃቸው በቤተሙከራ መረጋገጡን ይገልጻሉ። በቀጣይ ማከናወን የሚጠበቀው የአዋጭነት ጥናት በማድረግ የዲዛይን፣የቴክኖሎጂና የፋብሪካዎች የቦታ መረጣ ሥራ ማከናወን መሆኑን ያብራራሉ።

በሚኒስቴሩ እየተሠራ ያለው ሥራም ሆነ ሃገር ውስጥ ያለው ሀብት የብረት ኢንዱስትሪዎችን የሚመግብ፣ የግንባታው ዘርፍ የሚያጋጥመውን የግብዓት አቅርቦት ችግር የሚፈታ መሆኑንና ይህም ተስፋ እንደተጣለበት ነው ያመለከቱት።

የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዋልታ የሆነው የግብርናው ዘርፍም በማዕድን ሀብት የግብዓት ውጤት የሚታገዝ በመሆኑ በዚህ ረገድም ሚኒስቴሩ ትኩረት መስጠቱን ነው ሚኒስትሩ የተናገሩት። ማዳበሪያ ለማምረት የሚያስፈልጉ እንደ ካልሽየምና ፎስፌት ያሉ ጥሬ ግብአቶች በምዕራብ ኢትዮጵያ የሰልፈርና ፖታሽ ክምችት ደግሞ በሰሜን ምሥራቅ ኢትዮጵያ እንደሚገኝ ተረጋግጧል ሲሉ ጠቁመዋል።

አሞኒያን ለማምረት የሚያስፈልገው የተፈጥሮ ጋዝ ክምችት የማጥናትና የማረጋገጥ፣ተስማሚ ቴክኖሎጂ የመለየትና የኢንቨስትመንት አዋጭነት ጥናት ሥራም እየተሠራ መሆኑን ነው የተናገሩት። የክምችት መጠን ግመታና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት ግምገማ እንዲካሄድም ዓለም አቀፍ የአማካሪ ጨረታ በማውጣት ከዓለም አቀፍ ኩባንያ ጋር የስምምነት ውል መፈጸሙንና ኩባንያው ይህን ሥራውን በአራት ወር አጠናቅቆ እንደሚያስረክብም ጠቁመዋል።

የማዕድን ሀብት በሁሉም የሃገሪቱ ክፍል የሚገኝ በመሆኑ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር መሥራት ካልተቻለ የሚኒስቴሩ ጥረት ብቻውን ከዳር እንደማያደርስ ይታወቃል። ሚኒስቴሩም ይህን ታሳቢ በማድረግ ከክልሎች በተለይም የማዕድን ሀብት በስፋት ከሚገኝባቸው የክልል ፕሬዚዳንቶችና የሥራ ኃላፊዎች ጋር በቅርበት እየሠራ መሆኑን ነው ሚኒስትሩ የተናገሩት። ግንኙነቱ መጠናከሩ ለኮንትሮባንድ ንግድ ለተጋለጠው የማዕድን ዘርፉ፣ በዘርፉ ለሚሠማራው ባለሀብት የፀጥታ ሥጋት እንዳይኖር ለማድረግ፣በአጠቃላይ የተደራጀ የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ለመሥራት ያግዛል ብለዋል።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ በእስካሁኑ የጋራ እንቅስቃሴም የወርቅ ምርት ኮንትሮባንድን ለመከላከል፣እንዲሁም በተለያየ ምክንያት ምርት ያቆሙ የማዕድን ኩባንያዎች ወደ ሥራ የማስገባት ተግባርም ከክልሎችና ከፀጥታ ተቋማት ጋር በትብብር መሥራት በመቻሉ መሻሻል ታይቷል።

ሚኒስቴሩ የማዕድን ዘርፉ ከሚገኝበት ውስብስብ ችግር ውስጥ ወጥቶ ለሃገር ኢኮኖሚ አበርክቶ እንዲኖረው ጥረት ሲደረግ ነገሮች አልጋ ባልጋ እንዳልሆኑም ይታወቃል። የማዕድን ዘርፉ በስፋት በሚገኝባቸው አካባቢዎች የፀጥታ ችግር መኖሩ፣ ሥራዎች የተከናወኑት በዘርፉ የሰለጠነ በቂ ባለሙያ አለመኖርና የመሳሰሉትን ተግዳሮቶች በመቋቋም ጭምር እንደሆነ ሚኒስትሩ በሪፖርታቸው አቅርበዋል። ክፍተቶቹን ለመሙላትም ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ከፀጥታ አካላት ጋር በጋራ በመሥራት ጥረት እያደረገ መሆኑን ነው ያስረዱት።

ሚኒስቴሩ በነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ፣በወርቅ ምርትና ፍለጋ ሥራ ላይ ተሠማርተው በእቅዳቸው ባልተጓዙት ላይም እርምጃ በመውሰድ ሥራውን የማስተካከል ተልዕኮውን መወጣቱን አስታውቀዋል። ከነዚህ ውስጥም የተፈጥሮ ጋዝ ልማት ላይ የተሰማራው ፖሊ ጂሲኤል የተባለ ኩባንያ፣የወርቅ ምርት ፈቃድ የወሰደው ኬፊ ሜኔራልስ(ቱሉ ካፒ)፣የመጨረሻ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እንደተሰጣቸው አመልክተዋል።

ፓሊ ጂሲኤል አራት የፍለጋ አንድ የልማትና ምርት ፈቃድ እንዳለው ጠቅሰው፣ ኩባንያው ፈቃድ ወስዶ በሠራባቸው 9 ዓመታት የሚጠበቅበትን ሥራ አለማከናወኑ በግምገማ መረጋገጡን አስታውቀዋል። በዚህም ሕዝብና መንግሥት ከፍተኛ ተስፋ የጣለበትን የተፈጥሮ ጋዝ ልማት በተያዘለት ጊዜ እውን እንዳይሆን እንቅፋት መፍጠሩን ያመለከቱት ሚኒስትሩ፣ ኩባንያው ያለበትን የፋይናንስና የቴክኒክ አቅም ውስንነት እስከ በጀት ዓመቱ ማጠናቀቂያ ድረስ ካላሟላ ስምምነቱ የሚቋረጥ ስለመሆኑ የመጨረሻ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እንደተሰጠው ተናግረዋል።

ሚኒስትሩ በአፋር ክልል ዳሎል የፖታሽ ማዕድን ለማልማት ሚራክል ያራ ዳሎል እና ሰርከም ሚኒራልስ የተባሉ ሶስት ኩባንያዎች የሥራ ፈቃድ ቢወስዱም፣ በመሠረተ ልማት አለመሟላት ሥራቸውን እያከናወኑ አለመሆናቸውንም ለምክር ቤቱ ገልጸዋል። እንደ መንገድና መብራት ያሉ መሠረተ ልማቶችን ማሟላት ከሚኒስቴሩ አቅም በላይ መሆኑን ጠቅሰው የምክር ቤቱን እገዛ ጠይቀዋል።

የሚኒስቴሩን ሪፖርት ያደመጡት የምክር ቤቱ አባላት የተለያዩ ጥያቄዎችንና አስተያየቶችን አንስተዋል። ከቀረቡት ጥያቄዎች መካከልም በግንባታው ዘርፍ በተለይም የግንባታ ግብዓቶችን መጠንና ሥርጭትን ለመጨመር ስለተሠሩ ሥራዎች፣ብዙ ኢንቨስትመንትና የገንዘብ አቅም የማይጠይቁ በቀላሉ ማምረት በሚቻልባቸው እንደ አሸዋ ያሉ የማዕድን ግብአቶች ላይ የሚስተዋለው የዋጋ ንረት ከምን የመነጨ ነው ሲሉ ጠይቀዋል።

የሃገር ውስጥ የብረታብረት ኢንዱስትሪ ልማት በጣም ደካማና ኢኮኖሚውን የማይደግፍ ሆኖ ስለመቆየቱና ያለውን የብረት ማዕድን ሀብት በተደራጀና በተቀናጀ ለመጠቀም እየተሠራ ስላለው ሥራ፣የሲሚንቶ ፋብሪካዎች የማምረት አቅም ከ58 በመቶ በላይ ያለመብለጡና የዋጋ ንረትን የሚያስከትሉ ሰው ሠራሽ ችግሮች የመኖራቸው ጉዳይ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እንዴት እየታዩ መሆናቸውን የተመለከቱ ጥያቄዎችም ቀርበዋል፡፣ማዕድን ፍለጋ ላይ ለሚሠማሩ ኩባንያዎች ፍቃድ ከመሰጡ በፊት የመሥራት አቅማቸውን ለመለካት የተቀመጠው መስፈርት ምን ያህል የተጠና ነው የሚሉ ጥያቄዎች ቀርበዋል።

ሚኒስትሩም ጥያቄዎቹንና አስተያየቶቹን ተገቢነት ያላቸው ሲሉ ገልጸው፣ ማብራሪያዎችን ሰጥተዋል። አብዛኞቹን አስተያየቶችንም ሚኒስቴሩ በግብዓትነት ወስዶ እንደሚሠራባቸው አስታውቀው፣ የምክር ቤቱንም ድጋፍ የሚጠይቁ፣በፖሊሲና በአዋጅ የሚፈቱ ጥያቄዎም እንዳሉ ተናግረዋል።

ሚኒስትሩ ምክር ቤቱ ቢገነዘበው ባሏቸው ላይም ማብራሪያ ሰጥተዋል። እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ሃገር ውስጥ ያለው የድንጋይ ከሰል ጥራት የለውም በሚል ከውጭ እንዲገባ ግፊት ይደረግ ነበር። በተግባር ሲረጋገጥ ግን የሃገር ውስጥ የከሰል ድንጋይ ከውጭ ከሚገባው የድንጋይ ከሰል የሚበልጥ እንጂ የሚያንስ ሆኖ አልተገኘም። በሚሊዮን በሚቆጠር ዶላር ወጭ እየወጣ ወደ ሃገር ውስጥ እንዲገባ ሲደረግ የነበረው አላግባብ ነው። ይሄን መስመር የማስያዝ ሥራ እየተሠራ ነው።

ብረትን በተመለከተም እንደተናገሩት፤ በሃገር ውስጥ 18 የብረት ፋብሪካዎች ይገኛሉ። ፋብሪካዎቹ የኢትዮጵያን ማዕድን ፈልገውና አምርተው እንዲያቀርቡ በሚል አይደለም የተገነቡት። ከውጭ የሚገቡ ብረቶች ላይ አነስተኛ ነገሮች በመጨመር ነው ለገበያ ሲያቀርቡ የቆዩት። «ሁሉም ነገር ከውጭ ይገባል። የሃገራችንን ሀብት እንዳንጠቀም ነበር ሲደረግ የቆየው።

ትርክቶቻችን በተቀየሩ ቁጥር ሃገራዊ ሀብቶቻችንን የምናይበት አይናችን ሲከፈት ችግሮች ይወገዳሉ» ሲሉም ተናግረዋል። በአጠቃላይ ዘርፉ ሃገራዊ ምርት ላይ ባለመድረሱ ብዙ ብኽታዎች እንደሚኖሩም ገልጸዋል።

ሚኒስትሩ እስካሁን የደረሰባቸውን የማዕድን ሀብቶች ብቻ አዲስ ባቋቋመው የማዕድን ጋለሪ ለማስተዋወቅ ዝግጁ መሆኑንም አስታውቀዋል። ጊዜ የሚወስዱ የማዕድን ፍለጋና ልማት ሥራዎች እንዳሉም ጠቅሰው፣ ፀጋዎች መኖራቸውን ግን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል ነው ያሉት ሚኒስትሩ።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ውበት ሀሰት ነው

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ከእንቅልፏ ነቅታ ስልኳን ስታየው ማቲ አራት ጊዜ ደውሎ ነበር። ከዚህ በፊት እንዲህ እንደ አሁኑ በጠዋቱ ነቅታ ስልኳን ስታየው የምታውቀውም የማታውቀውም ብዙ ስልክ ተደውሎ ነበር የሚጠብቃት። አሁን ከማቲ በቀር ማንም የሚደውልላት የለም። እነዛ በውበቷ ተስበው ጠዋትና ማታ ስልኳን የሚያጨናንቁት ወንዶች አሁን ላይ ከውበት ሌላ ምንም እንደሌላት ሲያውቁ ሸሽተዋታል። ነፍስ ውበት ብቻ ከሆነች እንዲህ እንደ እሷ በትልቅ አለም ውስጥ ባይተዋር እንደሆነች አሰበች። ልብ ከትህትና እኩል ማፍቀርን ካልጨመረ፣ አእምሮ ከማሰብ እኩል ማገናዘብን ካልደመረ ሰውነት ትርጉም አልባ ነው ስትል ከአልጋዋ ላይ ተነሳች። ብዙ ሰዎች፣ ብዙ ታሪኮች፣ ብዙ መፈለጎች የከበቧት ነፍስ ራቁትነት ሲውጣት ህመሙ ምን ያክል እንደሆነ እያሰበች ወደ መታጠቢያ ቤት አመራች። ከሁሉም የሚበልጠው ህመሟ ግን ማቲም ውበት ብቻ ነሽ ብሎ ከተዋት ነው። ማቲ ፊት ውበት ብቻ ያላት ሴት እንዳትሆን የተቻላትን ሁሉ እየሞከረች ነው። አለም ላይ ውበት ብቻ እንደሆነች ሴት አስቀያሚ እንደሌለ ያወቀችው ሁሉም ከተዋት በኋላ ነው። ውበት ዋጋ የሚያወጣው በእውቀትና በምክንያታዊነት ሲታጀብ እንደሆነ የገባትን ያክል ምንም ገብቷት አያውቅም። ግን እንዴት ብላ ከውበት አስተሳሰብ መላቀቅ እንዳለባት አታውቅም። እንዴት ብላ ውበት ብቻ ያልሆነች ሴት መሆን እንዳለባት አታውቅም። እንዴት ብላ ውበቷ ውስጥ እውቀት፣ ሴትነቷ ውስጥ ትህትና ማብቀል እንዳለባት አታውቅም። የኖረችው ስለውበት ብቻ እያሰበች ነው። ያደገችው ውበቷ ሁሉን ነገር እንደሚሰጣት እየተነገራት ነው። ታዲያ ይቺ ሴት በአለም ላይ ለእሷ የሚሆን ምን ስፍራ አላት?

ከመታጠቢያ ቤት መልስ መስተዋቱ ፊት ተገተረች።

**መስተዋቱ ፊት በምታየው በራሷ ውበት መደነቅ ጀመረች። ልቅም ያለች ቆንጆ ሆና ፍቅረኛ ማጣቷ ሳቋን አመጣው። እንደ ዛሬ አናዳጅ ሳቅ ስቃ አታውቅም። እየተናደደች ሳቀች። ማሽላ ሲያር ይስቃል እንደሚባለው እያረረች ሳቀች**

ልቅም ያለች ቆንጆ ሆና ለምን መስተዋት እንደምትወድ ይሄም ይገርማታል። ፊቷን በመስተዋት ሳታይ፣ ጸጉሮቿ ላይ አርቴፊሻል ሳትቀጥል፣ አይኖቿን ቅንድቦቿን ሳትኳልና ሳትቀነደብ አንድ ርምጃ ተራምዳ አታውቅም። እንብርቷን ሳታሳይ፣ ገላዋን ሳትገልጥ ለብሳ አታውቅም። ታክሲ ላይ ሳትጨቃጨቅ፣ መንገድ ላይ ገፋኸኝ ብላ ከአንዱ ጋር ሳትሚገት ገብታ አታውቅም። ይሄ ባህሪዋ ከብዙ ጓደኞቿ ጋር ሲያጋጫት ነበር። ይሄ ባህሪዋ ቆንጆ ብቻ እንዳደረጋት ገና አልደረሰችበትም። ክብሯን ሀይለኝነት ውስጥ ነው ፈልጋ የምታገኘው። በትህትና መከበርን፣ በይቅርታ ከፍ ማለትን አታውቀውም። በመተው መብለጥን፣ አይቶ በማለፍ መላቅን አልደረሰችበትም። በቃ ከእውቀትና ከጥበብ የተኳረፈች ቆንጆ ብቻ ናት..

መስተዋቱ ፊት በምታየው በራሷ ውበት መደነቅ ጀመረች። ልቅም ያለች ቆንጆ ሆና ፍቅረኛ ማጣቷ ሳቋን አመጣው..እንደ ዛሬ አናዳጅ ሳቅ ስቃ አታውቅም። እየተናደደች ሳቀች። ማሽላ ሲያር ይስቃል እንደሚባለው እያረረች ሳቀች። ነፍስ በውበት ብቻ አትቆነጅም፣ ሰውነት በመልክ ብቻ አይጎመራም..ማሰብ የሌለበት ሰውነት ፍሬ እንደሌለው ዛፍ ነው ሲል ከየት እንዳመጣው እንጃ አእምሮዋ ሹክ አላት። ግን አትማርም..ግን ለመለወጥ አትዘጋጅም። ብትማር ኖሮ በውበቷ በኩል ገቡ በርካታ አስተማሪ ታሪኮች ነበሯት። ግን ራሷን መፈተሽ አትችልበትም።

መስተዋቱ ላይ እንዳፈጠጠች ራሷን ማሰማመር ጀመረች። አይኖቿን ኩላ፣ ቅንድቧን ስላ፣ እንብርቷን ያሳየ፣ ገላዋን የገለጠ ዘመነኛ ልብስ ለብሳ ማቲ ጋ ደወለች..

‹የኔ ፍቅር! ሲል ስልኩን አነሳው።

‹ስትደውልልኝ ተኝቼ ነበር..

‹እንቅልፋም..› አላት።

‹ቶሎ ነይልኝ ናፍቀሽኛል..

‹ምንም ብታወራ ከኔ የሚበልጥ ስሜት የለህም። የማፈቅርህ፣ የምናፍቅህ ከዚህ በኋላ በማይደገም ስሜት ነው› አለችው።

‹አንቺ በማይደገም እኔ ግን ሆኖ በማያውቅ የፍቅርና የናፍቆት ስሜት ነው የተጣበኩሽ› ሲል መለሰላት፡

‹ጉረኛ ነህ..

የኔ ፍቅር ቶሎ ነይልኝ…

‹እሺ እመጣልሀለው..እየወጣሁ ነው› ብላ ቶሎ ልትሄድለት ስልኩን ዘጋችው።

ዛሬ ቀኑን ሙሉ ከማቲ ጋር ነው የሚያሳልፉት። ቅዳሜ መጥቶ ሳይገናኙ ቀርተው አያውቁም። በተለይ ከሰአት ሲሆን ሁሉም ነገር ሌላ ነው። ከቤት ወጣች.. ከቤት ስትወጣ ስለራሷ እያሰበች ነበር። በዚህ ቁንጅናዋ ፍቅረኛ ማጣቷ ይገርማታል። ቁንጅናዋ ብዙ ነገር ሲሰጣት ታማኝ ወንድ ግን አልሰጣትም። ወደ ህይወቷ የመጡ ወንዶች ሁሉ እያፈቀረቻቸው የተለዩዋት ናቸው። ከውበቷ እኩል፣ ከሽቅርቅርነቷ እኩል ወንዶችን ሁሉ የሚያሸሽ የሆነ ያልደረሰችበት ጉድፍ ያላት ይመስላታል። ከአለባበሷ እኩል፣ ከዝነጣዋ እኩል የቀረባትን ሁሉ የሚያርቅ የሆነ ገፊ ተፈጥሮ ያላት ይመስላታል። እንደዛ ባይሆን እማ በዚህ ልክ በፍቅር ርሀብ አትራቆትም ነበር። እንደዛ ባይሆን እማ በዚህ ልጅ በወንድ ልጅ አትቀጣም ነበር። ከሁሉ በኋላ የፍቅር ትርጉሙ፣ የመኖር እጣ ፈንታው ይሰወርባታል። ነፍስ ፍቅር ከሌላት ዋጋዋ ምንድነው? ስትል ራሷን ትጠይቃለች።

በግንኙነቷ በራሷ ላይም ሆነ በሌሎች ላይ ጥፋት ላለመስራት ሳትደነቃቀፍ በዝግታ ለመራመድ ሞክራ ታውቃለች። ግን ስህተት ላለመስራት በዝግታ የተራመደችባቸው መንገዶች ሁሉ ያዳለጧት ነበሩ። ወደ ህይወቷ የመጣን ወንድ ለማቆየት ስትል በዝግታ አስባ፣ በጥንቃቄ አውርታ ታውቃለች። በፍቅር ርሀብ የጠወለገች ነፍሷን ለማለምለም ስትል ሁሉንም እሺ፣ ሁሉንም ልክ ነው ስትል ተቀብላ ነበር። እየቀረቡ የሚሸሿትን ወንዶች ለማኖር ስትል ያልሆነችውን ሆና ነበር። እነዚህ ሁሉ ግን የምትፈልገውን ሊሰጧት አልቻሉም። ከብዙ ፍለጋና ከብዙ እንግልት በኋላ ማቲ ከሚባል ልጅ ጋር ተዋወቀች። ማቲ ወደ ህይወቷ እስከገባበት ጊዜ ድረስ የፍቅር ድርቅ መቷት ነበር። አሁን ማቲን ላለማስቀየም፣ ማቲን ላለማስከፋት ስትል ነው የምትኖረው።

የሰው ልጅ በውበቱ ውስጥ ጥበብ፣ በሰውነቱ ውስጥ ርህራሄ ከሌለው አውሬ ነው። የሰው ልጅ በልቡ ውስጥ ፍቅር፣ በአእምሮው ውስጥ በጎ ሀሳብ ከሌለው እንስሳ ነው። ሰው ከአካላዊ ስልጣኔ ርቆ አእምሮአዊ እስካልሆነ ድረስ ከውበት ባርነት መላቀቅ አይችልም ስትል በራሷ ነውር ራሷ ላይ ፈረደች። በቀጣይ ህይወቷ ሴት ሆና፣ በውበት ውስጥ ሳይሆን በእውቀት ውስጥ ለመፈጠር እየማለች ከቀጠሯቸው ቦታ ደረሰች። እዛ ስትደርስ ማቲ አልነበረም..ልትደውልለት ስልኳን ስትጎረጉር..

የሆነ እጅ ከኋላ በኩል ፊቷ ላይ አርፎ ‹ማነኝ? አላት

ማቲ እንደሆነ አውቃለች…ደስ አላት። ለዚህ ሰው ስትል ራሷን አፍርሳ መስራት አለባት..ማቲ ከተዋት ሰው እንደማትሆን ታውቃለች። እጁን ከፊቷ ላይ አንስቶ ደረቱ ላይ ሲያሳርፋት አካሏን ጥላ በአእምሮዋ ለመኖር ለራሷ እየማለች ነበር።

# ዓለም አቀፍ

## የሩሲያ ወታደሮች ሰቭሮዶነስክ ከተማን ለመያዝ ተቃርበዋል

ወራትን ባስቆጠረው የሩሲያና ዩክሬን ጦርነት ወደ ሰቨሮዶንስክ ከተማ የሚወስደውን አውራ ጎዳና ለመቆጣጠር ኃያል ጦርነት እየተደረገ ነው።

ሩሲያ ይህን ከተማ ለመቆጣጠር ተቃርቤያለሁ ብትልም አንድ ከፍተኛ የዩክሬን ባለሥልጣን ነገሩን አስተባብለዋል።

ይህ ጎዳና ዩክሬን የምትቆጣጠራቸውን ከተሞች ሩሲያ ከያዘቻቸው ከተሞች ጋር የሚያገናኝ ከፍ ያለ ወታደራዊ ዋጋ ያለው ነው።

“ሉሃንስክ አልተቆረጠችም” ብለዋል። ሰርሂይ ሃይዳይ የተባሉ የዩክሬን ወታደራዊ ባለሥልጣን

አሁን ጦርነቱ እየተደረገ ያለው በምሥራቁ ክፍል ሰቨሮደንስክ ከተማ አቅራቢያ ነው።

ከተማዋን ለመቆጣጠር ታዲያ የባክሙት አውራ ጎዳናን መያዝ በቂ ነው።

ጦርነቱ ያየለውም ለዚሁ ነው።

እኚሁ የዩክሬን ባለሥልጣናት ይህን ቁልፍ መንገድ ለመያዝ ከፍ ያለ ጦርነት እየተካሄደ እንደሆነ ግን አልሸሸጉም።

ሰቨሮዶንስክ በቀን ለ24 ሰዓት በአየርና በምድር ኃይል እየተደበደበች ትገኛለች። ማክሰኞ ዕለት በነበረ ጥቃት 6 ሰዎች ተገድለዋል ብለዋል።

ሩሲያ ከዚች ከተማ ቅርብ ያለችውን ሊቻንስክ ከተማን ከተቆጣጠረች ሙሉ የሉሃንስክ ከተማን በእጇ ታስገባለች ተብሎ ይጠበቃል።

የሉሃንስክ አካባቢ አስተዳዳሪ የሩሲያ ወታደሮች ንጹሃንን ዒላማ አድርገዋል ሲሉ ይከሳሉ።

በሰቨሮዶንስክ ብቻ 15ሺህ ነዋሪዎች በመጠለያ ውስጥ ይገኛሉ።

“ከተማዋን መቆጣጠር ሲያቅታቸው ከተማዋን ማጥፋትን መረጡ” ሲሉም ከሰዋል አስተዳዳሪው።

ሩሲያ በዩክሬን ወረራ ከከፈተች ሦስት ወራት ቢያልፍም ፈጣን ድል አልቀናትም።

የብዙ ወታደራዊ ተንታኞች ግምት ሩሲያ የምትፈልጋቸውን ግዛቶች በአጭር ጊዜ እጇ ከማስገባት የሚያቆማት ኃይል የለም የሚል ነበር።

ለሩሲያ ግስጋሴ መገታት አንዱና ዋንኛው ምክንያት የሩሲያ ወታደሮች የመዋጋት ፍላጎት ዝቅተኛ መሆንና በተቃራኒው የዩክሬን ወታደሮች በከፍተኛ ወኔ እየተዋጉ በመሆኑ ነው ይላሉ ተንታኞች።

ሩሲያ በዩክሬን ዋና ከተማ ኪየቭ አቅራቢያ ከበባ በመፈጸም በመጀመሪያዎቹ የጦርነቱ ሳምንታት ፈጣን ድል ታደርጋለች ተብሎ ሲጠበቅ ነው ጦርነቱን ሙሉ በሙሉ ወደ ምሥራቁ ክፍል ለማድረግ ከሰሜንና ምዕራብ ዩክሬን ያፈገፈገችው።

በዚህ ጦርነት ሩሲያ በሺህ የሚቆጠሩ ታንኮችና ወታደሮችን እንዳጣች እየተነገረ ነው።

የሩሲያ ብሔራዊ ቴሌቪዥን ትናንት ለመጀመሪያ ጊዜ ቭላድሚር ፑቲን ሞስኮ ሆስፒታል ሄደው የቆሰሉ ወታደሮችን ሲያነጋግሩ አሳይቷል።

በዚህ ለአጭር ሰዓት በቆየው ተንቀሳቃሽ ምሥል ፑቲን ለአንድ የቆሰለ ወታደር “አባትህ ባንተ ይኮራል”ሲሉ ይሰማል።

ፕሬዚዳንት ዘለንስኪ በበኩላቸው በምሥራቅ ዩክሬን ሁኔታዎች እጅግ እየከፉ መምጣታቸውን ተናግረዋል።

ሩሲያ ትኩረቷን ሙሉ በሙሉ ወደ ምሥራቅ ብታደርግም ከትናንት በስቲያ ከባድ የተባለ የሚሳይል ጥቃት ወደ ደቡባዊቷ ከተማ ዛፖሪሺያ አስወንጭፋለች።

ከ60 በላይ ቤቶችና የገበያ ማዕከላትንም አውድማለች።

ቭላድሚር ፑቲን፣ ሩሲያ አሁን ከዩክሬን በያዘቻቸው አካባቢዎች ያሉ ነዋሪዎች የሩሲያን ፓስፖርት በቀላሉ እንዲያገኙ የሚያስችል ረቂቅ ሕግ አጽድቀዋል።

ይህም ሩሲያ በረዥም ጊዜ ዩክሬንን ለማጠቃለል ያላትን ትልም ያሳበቀ ሆኗል።

በ2014 ከሩሲያ ቁጥጥር ሥር የዋሉት ዶኔስክ እና ሉሃንስክ አካባቢዎች ራሳቸውን የሩሲያ ሪፐብሊክ አድርገው ነው የሚመለከቱት።

ሩሲያ በዚህ አካባቢ ለሚኖሩ ስምንት መቶ ሺህ ነዋሪዎች ፓስፖርት አድላለች።



## ከአፍሪካ ጋር ያላት ትብብር በዲፕሎማሲው መስክ ሁልጊዜ ቅድሚያ የምትሰጠው መሆኑን ቻይና ገለጸች

አዲስ አበባ ፡- ቻይና በዲፕሎማሲዋ ቅድሚያ የምትሠጠው ከአፍሪካ ጋር በትብብር መሥራት መሆኑን የሀገሪቷ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዋንግ ዪ ገለጹ።

ዋንግ ዪ ይህን ያሉት በቤጂንግ በተከበረው 58ኛው “የአፍሪካ ቀን” ክብረ-በዓል ላይ ነው።

በአውሮፓውያኑ የቀን አቆጣጠር 1963 የተቋቋመው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ምሥረታ የሚታሰብበት “አፍሪካ ቀን” እየተከበረ ይገኛል። ዋንግ ዪ “የአፍሪካ ቀን” የአፍሪካ ብቻ ሳይሆን አንድነታችንን እና ትብብራችንን የሚያንጸባርቅ የእኛም ቀን ነው ብለዋል።

ሚኒስትሩ፥ ቻይና እና አፍሪካ ለሉዓላዊነታቸው እና ለነጻነታቸው ብሎም ለክብራቸው መታገላቸውን አውስተው፥ በቀጣይም እርስ በእርስ በመደጋገፍ ጥቅማቸውንና የልማት ፍላጎቶቻቸውን ያሳካሉ ብለዋል።

የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተከሰተበት ወቅት ቻይና እና አፍሪካ ወረርሽኙን ለመቋቋም በትብብር መሥራታቸውንም አስታውሰዋል።

በተጨማሪም ቻይና ለ12 ተከታታይ ዓመታት ትልቋ የአፍሪካ የንግድ አጋር ሆና መቆየቷንም ነው የተናገሩት።

የ“ቤልት ኤንድ ሮድ ኢኒሼቲቭ የቻይና እና የአፍሪካ ግንኙነት ሥር እንዲሰድ ያስቻለና ውጤታማ ፕሮጀክት መሆኑንም በንግግራቸው አንስተዋል።

በቀጣይም የቻይና -አፍሪካ ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ማደግ እንዳለበትና ትብብሩ በዓለምአቀፋዊ ጉዳዮች ላይም በተግባር መንጸባረቅ እንደሚገባው ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ መግለጻቸውን ሲጂቲ ኤን ዘግቧል።

# ስፖርት





## የእድሜ ጉዳይ- የአፍሪካ እግር ኳስ ነቀርሳ

ቦጋስ አበበ

አፍሪካ በእግር ኳስ ትልቅ አቅም ያላት አህጉር ብትሆንም እንደ ሌሎቹ አህጉራት ትልቅ ደረጃ መድረስ አልቻለችም። ለዚህም በርካታ ምክንያቶች ይቀመጣሉ። ለአፍሪካ እግር ኳስ እንቅፋት ብለው ባለሙያዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች ከሚያስቀምጡት ምክንያት አንዱ በትክክለኛው እድሜ ተሰጥኦ ያላቸውን ታዳጊና ወጣት ተጫዋቾች በበቂ ሁኔታ አለማፍራት ነው። በተለይም የእድሜ ማጭበርበር ጉዳይ በአፍሪካ የተለያዩ ውድድሮች የተለመደና መፍትሔ ያልተገኘለት መሆኑ የአህጉሪቱን እግር ኳስ እድገት እየጎተተው እንደሚገኝ ብዙዎች ያምናሉ። ካፍ በታዳጊና ወጣቶች በሚያካሂዳቸው ውድድሮች ይህን የእድሜ ማጭበርበር ጉዳይ ለመቆጣጠር የተለያዩ የእድሜ መመርመሪያ ቴክኖሎጂዎችን ሲጠቀም ቢስተዋልም ችግሩን ማስቀረት አልቻለም። በዚህም አስደናቂ ተሰጥኦ ይዘው ወደ ፊት ትልቅ ደረጃ የመድረስ ተስፋ ያላቸው ታዳጊዎች በእድሜ የበላዮቻቸው ተውጠው ሕልማቸው ሲጨልም ማየት የተለመደ ሆኗል። ይህ ችግር እግር ኳሳቸው ዳዴ እያለ በሚገኝ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሃገራት ብቻም ሳይሆን የተሻለ ደረጃ ላይ በሚገኙ የአፍሪካ አገራት ጭምር በስፋት መስተዋሉ የአህጉሪቱ እግር ኳስ ላይ ተስፋ እንዳይጣል ያደርጋል።

የደቡብ አፍሪካ እግር ኳስ ማኅበር ፕሬዚዳንት ዶክተር ዳኒ ጆርዳን፣ ሰሞኑን ለመገናኛ ብዙኃን በሰጡት አስተያየት የእድሜ ማጭበርበር ጉዳይ የአፍሪካን እግር ኳስ ወደ ኋላ እየጎተተው እንደሚገኝ ተናግረዋል። የአህጉሪቱን እግር ኳስ ከሌሎች አህጉራት ጋር ተፎካካሪ ሆኖ እንዲወጣ ከተፈለገም አሰልጣኞች የእድሜ ጉዳይ ላይ



በእድሜ ማጭበርበር ምክንያት በርካታ አፍሪካውያን ታዳጊዎች የመታየት እድል እያገኙ አይደለም፣

ትኩረት አድርገው መሥራት እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

እንደ ዶክተር ዳኒ ገለጻ፣ አፍሪካ ፊፋ በታዳጊና ወጣቶች መካከል የሚያካሂዳቸውን ሁሉንም ውድድሮች ማለት ይቻላል አሸንፋለች። አፍሪካ ኦሊምፒክን ጨምሮ፣ከ17ና20 ዓመት በታች የዓለም ዋንጫ ውድድሮችን አሸንፋ አሳይታለች፣ ይሁን እንጂ በዋናውና በአዋቂዎቹ የዓለም ዋንጫ ከግማሽ ፍጻሜ ተፋላሚነት የዘለለ ታሪክ የላትም። ይህም የሆነው አፍሪካ በታዳጊና ወጣቶች ውድድር ላይ ከእድሜ በላይ ተጫዋቾችን በማሰለፏ ነው። በታዳጊ ውድድሮች አዋቂዎች ይጫወቱና ስኬታማ ይሆናሉ። ከዚያ ወደ አዋቂዎች ውድድር ሲሸጋገሩ አቅምና ጉልበታቸውን ጨርሰው በትክክለኛ እድሜ የብቃታቸው ጥግ ላይ ከሚገኙ የሌሎች አህጉራት ተጫዋቾች ጋር መፎካከር ይሳናቸዋል።

ይህን የእድሜ ችግር በቅርቡ በዲሞክራቲክ ኮንጎ ኪንሻሳ ላይ በተካሄደው የፓን አፍሪካ የትምህርት ቤቶች ውድድር ላይም እንዳስተዋሉ የሚናገሩት ዶክተር ዳኒ፣ ለዚህም በታዳጊ ወጣቶች ላይ የሚሠሩ አሰልጣኞችን ዋነኛ ተጠያቂ ያደርጋሉ።

የአንድ ሃገር የወደፊት እግር ኳስ ስኬት ያለው በትምህርት ቤቶች በሚገኙ ታዳጊዎች ላይ መሆኑን የጠቆሙት ዶክተር ዳኒ፣ ከእድሜ ማጭበርበር ጋር በተያያዘ ያለውን ችግር ፊት ለፊት አውጥቶ በመነጋገር መፍትሔ ማበጀት እንደሚያስፈልግ ያምናሉ። ለዚህም አሰልጣኞች ችግሩን በቅርበት ተከታትለው እንዲቀርፉ የአሰለጣጠን መንገዶችን ማስተካከል አስፈላጊ መሆኑን ይናገራሉ። እግር ኳሳቸው ባደገ እንደ አውሮፓ ባሉ ሃገራት አንድ የታዳጊ አሰልጣኝ ለሃያ ተጫዋቾች ነው የሚመደበው፣ እንደ አፍሪካ ባሉ አገራት ግን ብዙ ጊዜ አንድ አሰልጣኝ ሁለት መቶ ታዳጊዎችን ሊያሰለጥን የሚችልበት ሁኔታ መኖሩ ችግሩን ለመቆጣጠር አስቸጋሪ እንዳደረገው ዶክተር ዳኒ ያብራራሉ።

እግር ኳስ ትልቅ የገቢ ምንጭ እየሆነ በመጣበት በዚህ ወቅት በአፍሪካ ከአሰልጣኞች በተጨማሪ የተጫዋቾች ወኪሎች በአቋራጭ ጥቅም ለማግኘት በታዳጊ ውድድሮች አዋቂዎችን ማበረታታቸው ችግሩን ውስብስብ እንዳደረገው ሚስጥር አይደለም። ለዚህም ተጫዋቾች የተለያየ ሁለት እድሜ ይለጠፍባቸዋል። በርካቶቹ የአውሮፓ ክለቦችም ተሰጥኦ ያላቸው ታዳጊዎችን ለመመልመል በዚህ እንደሚቸገሩ ይታወቃል።

“እድሜ ማጭበርበር የአፍሪካን እግር ኳስ መግደል ነው” የሚሉት የግብጽ እግር ኳስ ማኅበር የሚዲያ ኦፊሰር ሜድሃት ሻላቢ እድሜ ማጭበርበርን በአፍሪካ እግር ኳስ እንደ ካንሰር አድርገው ይገልጹታል። ይህ መጥፎ ልማድ የአፍሪካን እግር ኳስ እያጠፋው ነው የሚሉት ባለሙያ እድሜ የሚጭበረበር ከሆነ በተለያዩ ደረጃዎች የሚካሄዱ የታዳጊና ወጣት ውድድሮች ፋይዳ ምኑ ላይ ነው? ብለው ይጠይቃሉ።

የእድሜ ማጭበርበር ችግሮችን ለመቅረፍ ፊፋ እኤአ በ2009 ከ17 አመት በታች የዓለም ዋንጫ ጀምሮ ማግኔቲክ ሪሶናንስ ኢሜጂንግ(ኤም አር አይ) የተባለውን ቴክኖሎጂ በተለያዩ የወጣት ውድድሮች ላይ ለመጠቀም መወሰኑ ይታወቃል። ይህ ቴክኖሎጂ እስከ 17 ዓመት ድረስ ያሉ ታዳጊዎችን ትክክለኛ እድሜ ለመለየት 99 በመቶ ስኬታማ ነው ቢባልም ከተጠቀሰው እድሜ በኋላ ለመለየት ሲቸገር ተስተውሏል። በኢትዮጵያም ታላቅን ታናሽ፣ ታናሽን ታላቅ አድርጎ የለየበት አጋጣሚ እንደነበር አይዘነጋም። ያም ሆኖ ቴክኖሎጂው አፍሪካ ውስጥ የእድሜ ጉዳይ አሳሳቢነቱን በተለያዩ ውድድሮች የተጭበረበሩ እድሜዎችን በማጋለጥ ማሳየቱ አይካድም።

የቅርቡን ለማስታወስ ያህል በ2020 የካፍ የወጣቶች ውድድር ኮሚቴ የዚምባቡዌ፣ኮሞሮስ፣ቦትስዋናና ሌሎች አገራት ብሔራዊ ቡድኖችን ከደቡብ አፍሪካ አገራት የ17 ዓመት በታች ዋንጫ ተሳትፎ በእድሜ ማጭበርበር ምክንያት ማገዱ ይታወቃል። በበርካታ አጋጣሚዎችና የታዳጊ እንዲሁም ወጣት የአፍሪካ ውድድሮች አገራት ሙሉ በሙሉ ባይታገዱ እንኳን በእድሜ ማጭበርበር ተጫዋቾቻቸው ከውድድሮች ያልተሰናበቱበት አጋጣሚ አይታወስም።

---


### ኦሮሚያ ክልል

ንብረትነቱ በአቶ ደኔ ጀማል የሆነ የተሽከርካሪ ዓይነት ባጃጅ የሠሌዳ ቁጥር 01-90592 ኦሮ የሆነ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ02/9/2014 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ስለዚህ የጠፋውን ሠሌዳ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት የያዘ በ15 ቀናት ውስጥ ባይመለስ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**የምሥራቅ ወለጋ ዞን ትራንስፖርት ባለሥልጣን**

የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2-A03675 ኦ/ሮ የሆነ ሰሌዳ ጠፍቶብኛል ብለው ባለንብረቱ አሚር ደሰታ በቀን 06/08/2014 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡ ስለሆነም ሰሌዳውን ወድቆ፣ ተሰርቆ ያገኘ በእዳ ወይም በሌላ ምክንያት ይገኛዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ሪፖርት እንዲያደርግ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ካላቀረበ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በምዕራብ አርሲ ዞን ትራንስፖርት ባለሥልጣን**

### የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ

ንብረትነቱ የአቶ ታረቀኝ ቡሩሴ የተሽከርካሪ ዓይነት አውቶቢስ የሰሌዳ ቁጥር 3-10342 ደ/ህ የፊት ሰሌዳ የጠፋ ስለ መሆኑ ገልጸዋል፡፡ ሰሌዳውን ወድቆ፣ ያገኘ በእዳ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሰባት ቀናት ውስጥ ሪፖርት እንዲያደርግ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ካላቀረበ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በ/ደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ የሀዲያ ዞን ትራንስፖርትና መንገድ ልማት መምሪያ**

የባለንብረቱ ስም አላሙዲን ሬድዋን የሰሌዳ ቁጥር 1-21785 ደ/ህ የሻንሲ ቁጥር md2a25bzdjwb82768 የሞተር ቁጥር azzwjbo3488 ከላይ የተጠቀሰው ተሽከርካሪ 1-21785 ደ/ህ የፊት ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ25/8/2014 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሰሌዳው ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀመሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍርድ ቤት ማሳገኛ ትእዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ታርጋ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**የጉራጌ ዞን ትራንስፖርትና መንገድ ልማት መምሪያ**

### አማራ ክልል

ንብረትነቱ በለጠ ተስፋዬ ኮድ 01-32710 አ.ማ ተሽከርካሪ ሰሌዳ የጠፋባቸው መሆኑን በመግለጽ ምትክ ሰሌዳ እንዲቀረጽላቸው በቀን 02/09/2014 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቀውናል፡፡ ስለሆነም ሰሌዳውን ወድቆ፣ ተሰርቆ ያገኘ በእዳ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ሪፖርት እንዲያደርግ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ካላቀረበ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአብክመ መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ የሰ/ሸዋ ዞን መንገድና ትራንስፖርት መምሪያ ብቃት ማረጋገጫ ቡድን**

ንብረትነቱ ይበልጣል ደስታው የሆነ አይሱዙ የተሽከርካሪ ሰሌዳ ኮድ 3-18874 አ.ማ ሰሌዳ የጠፋ መሆኑን ባለንብረቱ በ5/9/2014 በተፃፈ አመልክተዋል፡፡ ሰሌዳው ወድቆ ተሰርቆ ወይም በሌላ ግለሰብ እጅ ላይ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ሪፖርት እንዲያደርግ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የደቡብ ወሎ ዞን ትራንስፖርት ተጠሪ ጽ/ቤት የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ቡድን**

### አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ዘሩ ዳውድ በሽር የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A42722 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር JALK6A139G7102659 ሞዴል FSR6MS የሞተር ቁጥር 6HH1-488074 የሊብሬ ቁጥር 322686 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 8/9/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአራዳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ተስፋዬ መንግስቱ ወልዴ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-B82323 የተሽከርካሪው አይነት ድርብ አገልግሎት የሻንሲ ቁጥር AHIBA3CD503253113 ሞዴል GUN126L DNTHXWየሞተር ቁጥር 1GD-0862339 የሊብሬ ቁጥር 414459 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 8/9/2014 አመልክተዋል፡ ፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአራዳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ዘካሪያስ አህመድ አደም የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A52276 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር JAAKP34H5H7P02461 ሞዴል NPR6SN የሞተር ቁጥር 4HG1-598011 የሊብሬ ቁጥር 551183 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 1/2/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአቃቂ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ስመኝ ተሰማ ተካ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-4902 የተሽከርካሪው አይነት ሞተር ብስክሌት የሻንሲ ቁጥር MD634KE43F2B80298 ሞዴል APACHE RTR 160 የሞተር ቁጥር OE4BF2737969 የሊብሬ ቁጥር 142492 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 1/2/2014 አመልክተዋል፡፡ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የልደታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አህመድ ሠይድ አልዩ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-93210 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZAEBMEZHC222892 ሞዴል ZZ3161M4011W የሞተር ቁጥር WD615.87*070817005762* የሊብሬ ቁጥር 0179866 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 10/9/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የየካ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ዱግዳ አግሮ ኢንደስትሪ ኃላ/የተ/የግ/ማ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-68669 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር WJME3TRE2FC295928 ሞዴል A1380138H የሞተር ቁጥር F3BEE 681G*B220-228312 የሊብሬ ቁጥር 0096707 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 10/9/2014 አመልክተዋል፡ ፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአቃቂ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**